# የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረጃ መለኪያ

## (የተከለሰ)

*አዲስ ከተማ አስተዳዳር ትምህርት ቢሮ*

*ታህሳስ ወር 2005 ዓ.ም*

## ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ


1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረጃ መለኪያ (Standard) ……………… 1
1.1 የትምህርት ሥርዓት መዋቅር …………………………………..... 1
1.2 የት/ቤት ህንፃ አደረጃጀትና የአካባቢ ሁኔታዎች …………………… 2
1.2.1. የት/ቤት ህንፃ አሠራር …………………………………… 2
1.2.2. የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች ………………………….. 2
1.2.3. የምድረ ግቢ ገጽታ ………………………………………… 2
1.3የት/ቤት መጠን……………………………………………………
3
1.3.1. የክፍል መጠን አደረጃጀት……………………………….. 3
1.3.2. የምድረግቢ ሥፋት ……………………………………….. 3
1.3.3. የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መጠን …………………….. 4
1.3.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ላላቸው ት/ቤቶች …. 4
1.3.3.2. ሁለቱም ሳይክል ለያዙ /1-8/ ት/ቤቶች ……….. 4

1.4 አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶች ………………………………………
5
1.4.1. አንድ መማሪያ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ ቁሳቁሶችና መጠናቸው…. 5
1.4.2. 1-8 ክፍል ለቤተመጽሐፍት የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችና
መጠናቸው ………………………………………………
5 1.4.3. ከ1-8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለር/መምህራን፣ ለቢሮና ለመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚያስፈለጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት ……………………………………………
6 . 1.4.4. ከ1-8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለዕቃ ግምጃ ቤት
የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠብዛት……………………… 6

1.4.5.በመጀመሪያ ደረጃ የሳይንስ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ

እቃዎችና ብዛታቸው…………………………… 6
1.4.6. ለትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚያስፈልጉ መማሪያዎች. 7
1.5 የሰው ኃይል ምደባ ………………………………………………….
7
1.5.1.በየሳይክሉ ሊኖሩ የሚገቡ የተማሪዎች ብዛት…………….. 7
1.5.2. የተማሪ መጽሓፍት ጥምርታ …………………………… 8
1.5.3.የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ … 8
1.5.3.1. ለመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ………………………. 8
1.5.3.2. ለሁለተኛ ሳይክል /5-8/ …………………………. 8
1.5.3.3. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም ……………. 9
1.6 የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት ………………………………….. 9
1.6.1. የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት ……………………………….. 10
1.6.2. ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች ……………… 10
1.6.3. የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በትምህርት ዓይነት………………… 13

1.6.4. የትምህርት ቤት አመራር ሚና ................................ 14
1.6.5. የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም .............................. 16
1.6.5.1. የመምህራን የሥራ ሰዓት አጠቃቀም .............. 17
1.6.5.2. ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ ....................... 18
1.6.6. የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ፕሮግራም ....................... 19
1.6.6.1. የአእምሮ ውሱንነት ላላቸው /1-4/ ................ 19
1.6.6.2. ማየት ለተሳናቸው /1-4/ ............................ 19
1.6.6.3. መስማት ለተሳናቸው /1-4/ ........................ 20
1.6.6.4. የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል ................................................ 20
1.6.7. የሙሉ ቀን ትምህርት ፕሮግራም .......................... 21
1.6.8. የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም ............................... 21
1.6.9. የመማር ማስተማር መመሪያዎች ........................... 22
1.6.9.1. አጠቃላይ መመሪያዎች ............................. 22
1.6.9.2. የልዩ ፍላጎት ትምህርት መመሪያዎች ........... 22
1.6.9.3. ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች ...................... 23

1.7. የማስተማር ዘዴ (Teaching Methodology) ......................... 23
1.8. የትምህርት ምዘናና የማለፊያ ነጥብ ....................................... 24
1.9. የተማሪዎች ሚና (students' role)....................................... 25
1.10. የወላጆች ሚና (parents role ............................................ 26
1.11. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ የሚገባው ......................... 27
1.12. በትምህርት ሥራ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ .......................... 28
1.13. ልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ........................................ 28
1.13.1. የሬድዮ ትምህርት ................................................. 28
1.13.2. ቤተሙከራ ........................................................... 32
1.13.3. ቤተመጻሕፍት ...................................................... 32
1.13.4. የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት አደረጃጀት ................. 34
1.13.4.1. በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ የትምህርት ማበልፀጊያ የትም/መርጃ መሣሪያዎች ከማዘጋጀት አኳያ ለኖር የሚባው ስታንዳርድ .................. 35
1.13.4.2. በት/ቤት ማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የእጅ ሥራ መሥሪያ መሣሪያዎች ................. 35
1.13.4.3. ለየትም/ዓይነቱ ሊኖሩ የሚገባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ..................................... 35
1.13.5. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል ........................... 40
1.13.6. ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚያስፈለጉ የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት መሣሪያዎች .......................................... 42
1.14. የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ ስታንዳርድ ............................... 43
1.14.1. በየክፍል ደረጃውና በእየርከኑ የሚሰጡ የትም/ ማስረጃዎች ......................................... 43
1.15. በየእርከኑ መጨረሻ የሚጠበቁ የተማሪዎች ፕሮፋይሎች /ባህሪያት/. 44
1.15.1. የመጀመሪያ ደረጃ የ4 ዓመት ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ባህሪ .................................................. 44
1.15.2. የመጀመሪያ ደረጃ የ8 ዓመት ትምህርት ያጠናቀቀ

ተማሪ ባህሪ ……………………………………………….. 45

2

***መግቢያ***

*ትምህርት የዕድገት መሠረት ነው፡፡ ሰዎች የጠራ ራዕይ እንዲኖራቸውና ራዕያቸውንም ወደተግባር ለመለወጥ የሚያስችላቸውን አቅም የሚያጐለብት በመሆኑ ቀጣይነት ወዳለው የልማት ዕድገት የሚያሸጋግር ዋነኛ መሣሪያ ነው፡፡*

*የትምህርት ዓላማ የተቀመጠለትን ግብ ሊመታ የሚችለው በአንድ አገር የሚሰጠው ትምህርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡*

*የትምህርት ጥራት እንደየአገሮቹ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የተለያየ ቢሆንም እያንዳንዱ አገር ሊደርስበት የሚገባ የእድገት ደረጃ መሠረት ያደረገ የጥራት መለኪያ* (Standard) *ሊኖረው ይገባል፡፡*

*በአንድ አገር የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የትምህርት መለኪያ መኖር አስፈላጊነት የትምህርቱን ጥራት በተለያዩ መንገዶች ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ነው። ይህም የትምህርቱን አጠቃላይ ፕሮግራም በመፈተሽ ሥ/ትምህርቱን፣ የመምህሩን የማስተማር ዘዴንና የግምገማ ሂደትን፣ የመምህራን ሥልጠናንን እና የባለድርሻ አካላትን ሚና በመከለስ የትምህርቱን የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል በማድረግ ረገድ ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ ነው።*

*መንግሥታችንም ይህን እውነታ በውል በመገንዘብ ለትምህርቱ ዘርፍ የተለየ ትኩረት በመስጠት ትምህርትን ከማስፋፋትና ለሁሉም ዜጎች በእኩል ደረጃ ከማዳረስ በተጨማሪ የትምህርት ጥራት ጉዳይ የተሻለ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም በትምህርት ዙሪያ የሚታዩትን የጥራት ችግሮች ለማስወገድና ጥራቱን ለማስጠበቅ የጥራት ማስጠበቂያ ፓኬጅ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡*

*የትምህርቱ ዘርፍ ከተያዘለት ግብና ዓላማ አኳያ እየተካሄደ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥራት መለኪያ* (Standard) *በ*1987 *ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም ባለፉት* 16 *ዓመታት ውስጥ በትምህርቱ ዘርፍ ላይ በርካታ ለውጦች የተካሄዱ በመሆናቸው እነዚህን ለውጦች ማዕከል ያደረገ መለኪያ* (Standard) *ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡*

*ስለሆነም ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መለኪያ* (Standard) *እንደሚከተለው ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡*

## 1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረጃ መለኪያ (Standard)

**ዓላማ፡-**

- ❖ የትምህርቱ ዘርፍ መንግሥት ከቀየሰው የትምህርት ፖሊሲና የልማት ጐዳና ጋር አብሮ መጓዙን ለማረጋገጥ፣
- ❖ በየደረጃው የተማሪዎችን ብቃት ክህሎትና አመለካከት ለማወቅ፣
- ❖ በመንግሥት ለትምህርቱ ዘርፍ የሚመደበው የሰው ኃይልና በጀት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመገንዘብ፣
- ❖ በመንግሥትና በሌሎች ት/ቤቶች መካከል በትምህርቱ ዘርፍ ወጥ የሆነ የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ፣
- ❖ የአገራችን የትምህርት ጥራትና ደረጃ ከዓለም አቀፍ የትምህርት ጥራትና ደረጃ ጋር ያለው ትስስር ለመረዳት፣

### 1.1 የትምህርት ሥርዓት መዋቅር

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተከታተሉም ሆኑ ያልተከታተሉ ከ7 እስከ 14 ዓመት እድሜ ላላቸው ህፃናት በሁለት ሳይክሎች ማለትም 1ኛ ሳይክል ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች፣ 2ኛ ሳይክል ከ5ኛ - 8ኛ ክፍሎች ተከፍሎ የሚሰጥ ሆኖ በ8 ዓመታት ውስጥ የሚጠናቀቅ መሠረታዊ ትምህርት የሚሠጥበትና ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅ ነው፡፡ የልዩ ፍላጐት ትምህርትም ይህንኑ መሠረት ያደረገ አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡

**የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት፡-**

- ❖ ለተማሪዎች መሠረታዊ ትምህርትን በመስጠት አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ እድገትን ለማዳበር፣
- ❖ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተግባራትና ምርትን ለማስተዋወቅ፣
- ❖ ተማሪዎችን ለቀጣይ ትምህርት፣ ስልጠናና ለሥራ ዓለም የሚያዘጋጃቸው እውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን እንዲጨብጡ በማድረግ በደረጃው የምናፈራቸው ተማሪዎች ምርታማ፣ሥራ ፈጣሪና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ግንባታ የበኩላቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ማስቻል።

## 1.2 የት/ቤት ህንፃ አደረጃጀትና የአካባቢ ሁኔታዎች

### *1.2.1. የት/ቤት ህንፃ አሠራር*

በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልዳበሩ በመሆናቸው ምቹ የመማሪያ አካባቢ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ተማሪዎችን በብቃት ለማስተማር የት/ቤት ህንፃ ሁኔታና ት/ቤቱ የሚገኝበት አካባቢ አመቺነት፣ የተማሪዎችንና የመምህራን ብዛት መሠረት ያደረጉ የትምህርት ቁሳቁሶችን ማሟላትና የትምህርቱን ፕሮግራም አደረጃጀትንም አመቺ በሆነ መልክ ማደራጀት በተማሪዎች ተፈላጊ ባህሪያት ግንባታ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ስላላቸው በሥራ ላይ የሚገኙም ሆነ ወደፊት የሚከፈቱ ት/ቤቶች በብቃት መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ህንፃ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬትና ከሸክላ ወዘተ… ማቴሪያሎች ይሠራል።

### *1.2.2. የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች*

ተማሪዎች ከመኖሪያ ክልላቸው ከ 2 ኪሎ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ተመላልሰው መማር የሚችሉበት ሆኖ ት/ቤቱ የመማር ማሰተማር ተግባር ከሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ማለትም ከዋና መንገድ፣ ከአዋኪ ድምፅና ጫጫታ፣ ከመጥፎ ጠረን፣ ከመጠጥ ቤት፣ ከከፍተኛ ትራፊክ ፍሰት፣ ከወንዞችና ገደላማ ቦታዎች፣ ከገበያና ከፋብሪካ እንዲሁም የተማሪውን ስነምግባር ከሚያበላሹ ከቪዲዮ ቤቶችና ተለጣፊ ሱቆች ከመሣሰሉት የራቀ መሆን ይኖርበታል፡፡

### *1.2.3. የምድረ ግቢ ገጽታ*

- እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ምድረግቢው በድንጋይ፣ በብሎኬት፣ በእሾህ አልባ ሽቦና በእንጨት አጥር ሙሉ በሙሉ የታጠረና የተከበረ፣
- የመማሪያ ክፍሎች፣ የአስተዳደር ቢሮዎችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች እንደየሥራ ባህሪያቸውና እንደየአገልግሎታቸው አመቺነት የተሠሩ፣
- ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ የእግር መንገድ የተሠሩላቸው፣

- በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ /ሥፍራ/ ያለው፣
- ንፁሕ የመጠጥ ውሃ አገለግሎት ያለው፣
- የመዝናኛና መጫዎቻ ሜዳዎች ያሉት ሆኖ ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶችም ተመጣጣኝ ቦታ ያለው፣
- እንደአጠቃላይ የህንፃው አቀማመጥም ሆነ የግቢው ሁኔታ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ፣ ሳቢና ማራኪ የሆነ፣

## 1.3 የት/ቤት መጠን

የአንድ ት/ቤት መጠን በመማሪያ ክፍሎችና በሚኖሩት የተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ሲሆን የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ደግሞ በተማሪ ቁጥር ይወሰናል፡፡

የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ ክህሎትንና ትምህርትን ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችና ተስማሚ የሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች ማሟላት ይገባል፡፡

### *1.3.1. የክፍል መጠን አደረጃጀት*

አንድ ት/ቤት ለመጀመሪያ ደረጃ ለመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ቢያንስ **አራት** የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡ እንዲሁም ለሁለቱም ሣይክሎች /1-8/ ቢያንስ **ስምንት** የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

### *1.3.2. የምድረግቢ ሥፋት*

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ መማሪያ ክፍሎች ብዛት **ከ5000 ሜ.ካ. እስከ** 10,000ካሬ ሜትር የሚሆን የቦታ ስፋት ይኖረዋል፡፡ይህም ለት/ቤት ህንፃ፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ የጓሮ አትክልት ቦታና ለተማሪዎች የእረፍት ሰዓት መዝናኛና መጫወቻ እንደዚሁም ለመማሪያ ክፍል አደረጃጀት መሠረት ት/ቤቱ ሌሎች ተጨማሪ የመማሪያ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች እንዲኖሩት ያስችላል፡፡

ነገር ግን ይህ ቦታ መጠን በከተማና በገጠር እንደ ሁኔታው ሊለያይ ይችላል፤ በ ከተሞች የቦታ ጥበትን ለመቅረፍ የት/ቤቶች ሕንፃዎች በፎቅ ደረጃ ሊሠሩ ይችላሉ። እንዲሁም የእስፖርት መሥሪያ ቦታዎች ከአንድ ዓይነት አገልግሎት፣ሁለገብ አገልግሎት በሚሰጥ ሁኔታ 64×75=4800 ካ.ሜ እንዲሁም ትንሹ ሜዳ 10×20=200ካ.ሜ /ከአንድ የእስፖርት ዓይነት/ በላይ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገው

ይዘጋጃሉ።

- ለትምህርቱ ጥራት መጠበቅ ሲባል አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከ2000 ተማሪዎች በላይ ማስተናገድ የለበትም።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ስፋት ቢያንስ 10 ተማሪዎችን በአንድ ክፍል በማሰብ ከ36 እስከ 56 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

### *1.3.3. የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መጠን*

#### 1.3.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ላላቸው ት/ቤቶች

| ተራ ቁ. | ክፍሎች | ብዛት | የያንዳንዱ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል | 4 | ከ36- 56 ካ.ሜ | ቢያንስ በአንድ ክፍል 10 ተማሪዎች |
| 2 | የርዕሰ መምህር ቢሮ | 1 | 4x5 = 20 | |
| 3 | የመምህራን ትም/ክፍል | 1 | 4x4 = 16 | |
| 4 | የዕቃ ግምጃ ቤት | 1 | 3x3 = 9 | |
| 5 | የመፀዳጃ ቤት | 6 | 1.50x80 = 1.2 | 2 የመምህራንና ሠራተኞች 4 የተማሪዎች (የሴትና የወንድ ተማሪዎች) በተለያየ ሕንፃ የተሠራ |
| 6 | የትምህርት ማበልፀጊያ ክፍል | 1 | 7x15 = 105 | |
| 7 | የንባብ ቤት | 1 | 7x8 = 56 | |
| 8 | ሁለገብ የሣይንስ ክፍል | 1 | 7x15 = 105 | |
| 9 | የዘበኛ ቤት | 1 | 2.45x2.45 = 6.8 | |
| 10 | ለልዩ ትምህርት የመማሪያ ክፍሎች የመማሪያ ክፍል | | 4x7 = 28 | |
| 11 | የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል | | 4x3.5 = 14 | |
| 12 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል | 1 | 4x3 = 12 | |
| 13 | የፅዳት ሠራተኛ ክፍል | 1 | 1.21x2.7 = 3.27 | |

#### 1.3.3.2. ሁለቱም ሳይክል ለያዙ /1-8/ ት/ቤቶች

| ተራ ቁ. | ክፍሎች | ብዛት | የያንዳንዱ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመማሪያ ክፍል /1ኛ-4ኛ/ | 4 | ከ36-56 ካ.ሜ | 1-4 ክፍል 50 ተማሪዎች በክፍል |
| 2 | የመማሪያ ክፍል /5ኛ-8ኛ/ | 4 | | 5ኛ-8ኛ 40 ተማሪዎች በክፍል |
| 3 | የርዕሰ መምህር ቢሮ | 1 | 4.8x4.5 = 19.6 | |
| 4 | የፀሐፊ ቢሮ | 1 | 2.7x4.84 = 13.67 | |
| 5 | የመምህራን ክፍል /ስታፍሩም/ | 1 | 4.05x7= 17.67 | /ከ5ኛ-8ኛ ክፍል |
| 6 | የመምህራን ክፍል | 1 | 2.4x7.26=17.42 | ከ1ኛ-4ኛ ክፍል/ |
| 7 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል | 1 | 4.05x1.84 = 19.60 | |
| 8 | ዕቃ ግምጃ ቤት /ስቶር/ | 1 | 6.72x6.05 = 40.84 | |
| 9 | የጽዳት ሠራተኛ ክፍል | 1 | 1.21x2.7 = 3.27 | |
| 10 | መጸዳጃ ቤት ለመምህራንና ሠራተኞች<br>▪ የወንዶች<br>▪ የሴቶች | 1<br>1 | 3.63x4.05 = 14.7<br>2.7x3.63 = 9.8 | |
| 11 | የንባብ ክፍል | 1 | 12.1x6.92 = 83.73 | |
| 12 | የመጻሕፍት ማስቀመጫ /ስቶር/ | 1 | 2.42x6.77 = 16.38 | |
| 13 | ሁለገብ የሣይንስ ክፍል | 1 | 8x15=/ = 120 | ከ1ኛ - 4ኛ |
| 14 | ሁለገብ የሣይንስ ክፍል | | | ከ5ኛ - 8ኛ |
| 15 | የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል | 1 | 7x15 =105 | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች |
| 16 | የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል | 1 | 8x10 = 80 | ማዘጋጃ፣ ሰርቶ ማሳያና ማዋሻ ክፍል |
| 17 | መፀዳጃ ቤት /ለተማሪ/ | 8 | 90x1.20 = 1.08 | የብሎኩ መጠን 5.30 |
| 18 | የዘበኛ ቤት | 1 | 2.45x2.45 = 6.8 | 4.20 = 22.26 የሴትና የወንድ ተማሪዎች በተለያየ ሕንፃ የተሠራ |
| 19 | የልዩ ትምህርት መማሪያ ክፍሎች የመማሪያ ክፍል ስፋት | 2 | 4x7 = 28 | |
| 20 | የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል | 1 | 4x3.5 = 14 | |

## 1.4 አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶች

### *1.4.1. አንድ መማሪያ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ ቁሳቁሶችና መጠናቸው*

| ተራ | | መጠኑ በሴንቲ ሜትር | ምርመራ |
|---|---|---|---|

| ቁ. | | ከፍታ | ወርድ | ቁመት | ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዴስክ /የመቀመጫው/ | 45 | 10 | 74 | 25 | በ1 ዴስክ 2 ተማሪዎች ይቀመጣሉ |
| 2 | ጠረጴዛ | 80 | 74 | 100 | 1 | ለመምህሩ |
| 3 | ወንበር | 40 | 56 | 78 | 1 | ለመምህሩ |
| 4 | ጥቁር ሰለዳ | = | 500 | 120 | 1 | |
| 5 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | = | 50 | 100 | 1 | |

### *1.4.2 ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ለቤተመጽሕፍት የሚያሰፈልጉ ማቴሪያሎችና መጠናቸው*

| ተራ ቁ. | ዓይነት | ከፍታ | ወርድ | ቁመት/ ርዝመት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንበር | 40 | 56 | 74 | 40-80 | |
| 2 | ጠረጴዛ | 80 | 100 | 74 | 7-14 | |
| 3 | መጽሐፍ መደርደሪያ | 200 | 40 | 150 | 5-8 | |
| 4 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት | | | | 1 | መካከለኛ |

### *1.4.3 ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለርዕሰ መምህራን፣ ለቢሮና ለመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት፣*

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ከፍታ | ወርድ | ርዝመት | ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል | | ከ1ኛ - 8ኛ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ለር/መምህር ቢሮ የሚያስፈል ገው ብዛት | ለመምህራን ማረፊያ የሚያ ስፈልግ ክፍል ብዛት | ለር/መምህር ቢሮ የሚያስፈ ልግ ቢሮ ብዛት | ለመምህራን ማረፊያ የሚያ ስፈልግ ክፍል ብዛት | |
| 1 | ባለኪስ ጠረጴዛ | 80 | 150 | 74 | 1 | - | 1 | - | |
| 2 | ጠረጴዛ | 80 | 100 | 74 | 1 | 1 | 1 | 3 | |
| 3 | ወንበር | 40 | 56 | 78 | 5 | 6 | 7 | 18 | |
| 4 | የፋይል ማስቀ መጫ ቁም ሳጥን | 200 | 60 | 100 | 1 | - | 1 | - | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | መጽሐፍት መደርደሪያ | 200 | 40 | 100 | 1 | - | - | - | |
| 6 | ቁልፍ ያለው ቁም ሣጥን | 200 | 40 | 120 | 1 | - | 1 | 4 | |
| 7 | የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 40 | 50 | 100 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| 9 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት | - | - | - | 1 | 1 | 1 | 1 | |

<u>ማሳሰቢያ</u>

*በየሣይክሉ የመማሪያ ክፍል ቁጥር በጨመረ ልክ የዕቃዎቹ ብዛት በዛው ልክ ሊጨምር ይችላል፡፡*

*1.4.4 ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለዕቃ ግምጃ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት፣*

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ከፍታ | ወርድ | ርዝመት | ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ብዛት | ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጠረጴዛ ባለኪስ | 80 | 150 | 74 | 1 | 1 |
| 2 | ወንበር | 40 | 56 | 78 | 2 | 2 |
| 3 | መጽሐፍ መደርደሪያ | 200 | 40 | 100 | 4 | 16 |
| 5 | ቁምሳጥን | 200 | 40 | 150 | 1 | 4 |
| 6 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | - | - | - | 1 | 1 |

*1.4.5. በአንደኛ ደረጃ ሁለገብ የሳይንስ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ የዕቃዎች አይነትና ብዛታቸው፣*

| <u>ተራ ቁ.</u> | <u>የዕቃው ዓይነት</u> | <u>ብዛት</u> |
|---|---|---|
| 1. | የመምህሩ /ዲሞንስትሬሽን/ ጠረጴዛ | 1 |
| 2. | በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ የተማሪ ጠረጴዛዎች | 10 |
| 3. | ኩርሲዎች ወይም ወንበሮች | 50 |
| 4. | ጥቁር ሰሌዳ | 1 |
| 5. | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 2 |
| 6. | /ሰፋፊ/ መደርደሪያዎች/ ለሥራዎች ማስቀመጫ | 4 |
| 7. | ቁምሳጥን | 1 |
| 8. | የንብረት ማስቀመጫ /ትንሽ ክፍል | 1 |
| 9. | የሳይንስ ኪቶች | 2 |
| 10. | የውሃ መያዣ ጀሪካን | 1 |

*1.4.6. ለትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች*

| ተራ ቁ. | ዓይነት | ሳይዝ በሴንቲ ሜትር | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከፍታ | ወርድ | ቁመት/ ርዝመት | ብዛት | |
| 1 | ወንበር | 40 | 56 | 78 | 3 | |
| 2 | ጠረጴዛ | 80 | 74 | 100 | 3 | |
| 3 | መደርደሪያ | 150 | 40 | 150 | 1 | |
| 4 | የመሥሪያ ቤንች 2 የእንጨት ሥራ መሥሪያ | 6 | 70 | 100 | 3 | ከሞርስ ጋር |
| 5 | ጥቁር ሰሌዳ | = | 500 | 150 | 1 | |
| 6 | ማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | = | 100 | 200 | 1 | |
| 7 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት | = | = | = | 1 | መካከለኛ |

## 1.5 የሰው ኃይል ምደባ

### *1.5.1. በየሳይክሉ ሊኖሩ የሚገቡ የተማሪዎች ብዛት*

- ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ባለው ደረጃ በክፍል እስከ 50 ተማሪዎች ይመደባሉ፡፡
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ባለው ደረጃ በክፍል እስከ 40 ተማሪዎች ይመደባሉ፡፡
- የልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ህፃናትና ወጣቶች ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ከሆነ በክፍል ከ5 መብለጥ የለባቸውም፡፡
- በመደበኛ ት/ቤት በሚከፈት ልዩ ክፍል ውስጥ አንድ መምህር ከ10-20 የሚደርሱ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት ያስተምራል፡፡
- አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር በዚህ መጠን መወሰን አስፈላጊ የሆነው በትምህርት አሰጣጥና አቀባበል ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አኳያ የተሻለ ውጤት ለማምጣትና የትምህርት ፋሲሊቲዎችን በአግባቡ ለመጠቀም ሰለሚያስችል ነው፡፡
- በአንድ ት/ቤት ከሚገኙት ከመደበኛ ተማሪዎች ውስጥ ልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ህፃናት ብዛት በአማካኝ ከ5%-10% ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

### *1.5.2. የተማሪ መጻሕፍት ጥምርታ*

- ተማሪዎች በየእለቱ በሚቀስሙት ትምህርት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት አስፈላጊ የትምህርት ግብኣቶች ተሟልተው ሲቀርቡላቸው ነው፡፡ ከግብኣቶቹ መካከል የማስተማሪያ መጻሕፍት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰጠው ሥራ በአግባቡ ሊወጣ የሚችለው የተማሪ መጻሕፍት ጥመርታ 1፡1 መሆን ሲችል ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ተማሪ <u>ከየትምህርት ዓይነቱ አንዳንድ መጽሐፍ</u> ሊኖሩት ይገባል፡፡

### *1.5.3. የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ*

#### 1.5.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/

| ተራ ቁ. | የሠራተኛው ዓይነት | ብዛት | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|
| 1 | ርዕሰ መምህር | 1 | - በዲኘሎማ የተመረቀ/ች ሆኖ የርዕሰ መምህርነት ኮርስ የወሰደ/የወሰደች |
| 2 | ዩኒት መሪ | 1 | - በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 3 | መምህራን | - | - በዲፕሎማ የተመረቁ ሆነው ለደረጃው የሚሰጠውን የመምህርነት ሥልጠና የወሰዱ |
| 4 | ዘበኛ | 2 | - 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች |
| 5 | ተላላኪ | 1 | - 8 ክፍል ያጠናቀቀ/ች |
| 6 | የፅዳት ሠራተኛ | 1 | - 8ኛ ክፍል ጠናቀቀ/ች |
| 7 | ፀሐፊ | 1 | - በሴክሬታሪያል ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 8 | የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ | 1 | - በላይብራሪ ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |

#### 1.5.3.2. የሁለተኛ ሣይክል /5-8/

| ተራ ቁ. | የሠራተኛው ዓይነት | ብዛት | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|
| 1 | ርዕሰ መምህር | 1 | - በትምህርት አመራርና እቅድ ዝግጅት በዲግሪ የተመረቀ/ች |
| 2 | ምክትል ር/መምህር | 1 | " " " " |
| 3 | ዩኒት መሪ | 2 | - በማንኛውም የትምህርት መስክ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 4 | መምህራን | - | - በዲፕሎማ የተመረቁ |
| 5 | ፀሐፊ | 1 | - በሴክሬታሪያል ሳይንሰ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |

| ተራ ቁ. | የሠራተኛው ዓይነት | ብዛት | የትምህርት ደረጃ |
|---|---|---|---|
| 6 | የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ | 1 | - በላይብራሪ ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 7 | የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ | 1 | - በንብረት አያያዝ ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 8 | ዘበኛ | 2 | - 8ኛክፍል ያጠናቀቀ |
| 9 | ተላላኪ | 1 | - 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች |
| 10 | ፅደት ሠራተኛ | 1 | - 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች |

**ማሳሰቢያ**

ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ላሉ ት/ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር ከ1000 በላይ ከሆነ ምክትልር/መምህር ይመደባል

### 1.5.3.3. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም መምህራንና ሠራተኞችን በተመለከተ፣

| ተራ ቁ. | የሠራተኛው ዓይነት | የትምህርት ደረጃ | |
|---|---|---|---|
| | | /1-4/ | /5-8/ |
| 1 | መምህር | በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች | በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |
| 2 | የንግግር ወጌሻ | በቋንቋ ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች ሆኖ በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሥልጠና የወሰደ/ች | በዲፕሎማ በቋንቋ የተመረቀ/ች የልዩ ትምህርት ፍላጐት ሥልጠና የወሰደ/ች |
| 3 | ረዳት ወይም ሞግዚት | በልዩ ፍላጐት ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች | በልዩ ፍላጐት ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች |

## 1.6. የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት

ትምህርት ታቅዶና ታልሞ ከህፃናት እድሜ፣ የአካል ብቃት፣ የአእምሮ ብስለትና የመማር ዝግጁነት ጋር እየተገናዘበ በደረጃና በጊዜ ተመጥኖ የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡

ሥርዓተ ትምህርት በአንድ አገር የትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመሰርቶ የሚዘጋጅ ሲለበስ፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያ፣ መርጃ መሣሪያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ጽሁፎችና የማስተማር ዘዴዎችን ያካትታል፡፡

በመሆኑም በአገራችን አስፈላጊውን ደረጃ የጠበቀና በየትምህርት እርከኑ ተገቢውን የባህሪ ገጽታ ሊቀርጽ የሚችል ሥርዓተ ትምህርት በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በተገለጹት አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ ተዘጋጅቷል፡፡

የትምህርት ፕሮግራሙ የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡፡

- የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት፣
- የክፍል ጊዜ ሥርጭት በትምህርት አይነት፣
- የትምህርት ቤት አመራር ሚና፣
- የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም፣
- የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም፣
- የሙሉ ቀን ትምህርት ፕሮግራም፣
- የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም፣
- የተለየ ትኩረት የሚሹ የትምህርት አይነቶች፣
- የመማር ማስተማር መመሪያዎች፣

### 1.6.1. የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት

- የተለያዩ አገሮች ጥናት እንደሚያመለክቱት በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከ150-250 የትምህርት ቀናት አሉ፡፡ በዚህ መሠረት በኛ ሀገርም በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት የተዘጋጀው ከ203-206 ባሉት ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ታስቦ ነው፡፡ ስለዚህ በዓመት ውስጥ ከ203-206 የትምህርት ቀናት ይኖራሉ፡፡
- አንድ የትምህርት ዘመን በሁለት ሴሚስተር ይከፈላል፡፡
- መደበኛ የትምህርት ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ሆኖ 5 ቀናት ይይዛል፡፡
- አጋማሽ የሴሚስቴር ፈተናዎች እና ተከታታይ ግምገማዎች ቴስቶች በትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ይሰጣሉ፡፡
- የየሴሚስተሩ መጨረሻ ፈተናዎች በሴሚስቴሩ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃሉ፡፡
- ከ1ኛ ሴሚስቴር ፈተና በኋላ የአንድ ሣምንት የፈተናና የማረሚያ ውጤት ማጠናቀሪያ ጊዜ ይኖራል፡፡
- በብሔራዊ ፈተናዎችና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች የሚባክኑ የትምህርት ቀናት ቢኖሩ መካካስ ይኖርባቸዋል፡፡

### 1.6.2. ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ዕውቀቶችን በማስጨበጥ ለሚቀጥሉት ተከታታይ የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠና እርከኖች ብቁ የሚያደርግና መሠረት የሚጣልበት በመሆኑ፣ ለቋንቋዎች፣ ለሂሣብና ለተፈጥሮ ሣይንስ ትምህርቶች ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
- ለነዚህ የትምህርት ዓይነቶች ትኩረት ይሰጣል ሲባል ከሥርዓተ ትምህርት ከመማሪያ መጻሕፍት፣ የመምህሩ መመሪያ፣ ከትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦትና በክፍል ውስጥ ለተማሪው የሚደረገውን ጨምሮ የተሟላ የትምህርት አቀራረብ ድረስ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል፡፡
- መምህሩ ትምህርቱን በዓመት፣ በሴሚስተር፣ በሣምንት/ በቀንና በክፍለ ጊዜያት ከፋፍሎ፣ የሚጠቀምበትን ተስማሚ የአቀራረብ ዘዴ፣ ትክክለኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን፣ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች (Activities) በመምረጥና በማዘጋጀት ከቀረበ በኋላ ትምህርቱ ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ በተማሪው ዘንድ ማምጣቱን የመገምገሙ ሥራ በብቃትና በጥንቃቄ ያካሄዳል፡፡

**<u>ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠናን አስመልክቶ</u>**

ለአንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያ ሳይክል መምህርነት የሚሰለጥኑ መምህራን አሀዳዊ የክፍል አያያዝና አመራር ዘዴን የሚጠቀሙ ሲሆን አሰለጣጠናቸው የክላስተር ሞዳሊቲ መሠረት ያደረገ ሆኖ ቋንቋን፣ የህብረተሰብ ሣይንስን፣ ሂሣብንና የተፈጥሮ ሣይንስን እንዲሁም ኤስቴቲክስ በአማራጭነት በመያዝ ይሰለጥናሉ።

**<u>ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠናን አስመልክቶ</u>**

| ተራ ቁ. | በትኩረት መስክ የሚሰጡ ትምህርቶች | መግለጫ |
|---|---|---|
| 1 | ቋንቋ<br>▪ አማርኛ<br>▪ እንግሊዝኛ<br>▪ ብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋ | ሶስቱንም የተምህርት ዓይነቶች ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ፣ |
| 2 | ተፈጥሮ ሣይንሰ<br>▪ ባዮሎጂ<br>▪ ኬሚስትሪ<br>▪ ፊዚክስ | ሶስቱንም የትምህርት ዓይነቶች በተናጠልና በማቀናጀት በአጠቃላይ ሣይንሰ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ፡፡ |
| 3 | የህ/ሰብ ትምህርት<br>▪ ጂኦግራፊ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ▪ ታሪክ<br>▪ ሲቪክስ | ሶስቱንም የትምህርት ዓይነቶች በተናጠልና በማቀናጀት /ኅብረተሰብ ትምህርት/ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ፡፡ |
| 4 | ሂሣብ | ከሂሣብ ትምህርት ጋር ቅርበት ያላቸውን ትምህርቶች ለምሳሌ ፊዚክስና ኬሚስትሪ በተጨማሪ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ፡፡ |
| 5 | የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ | የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት እንዲያስተምሩና በተጨማሪም ሌሎች አግባብ ያላቸው ትምህርቶችንም ይወስዳሉ፡፡ |
| 6 | ሙዚቃና ሥነ ሥዕል | ሁለቱንም የትምህርት ዓይነቶች እንዲያስተምሩ ሆነው ይሠለጥናሉ፡፡ |

ከላይ የተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች በትኩረት መስክ ይሰጡ እንጂ የሠልጣኞችን አጠቃላይ ዕውቀት ለማሳደግ ያህል በተጨማሪ በጋራ (common) የሚወስዷቸው የትምህርት ዓይነቶች ይኖራሉ፡፡ <u>**ለምሳሌ፡**</u>- ፔዳጐጂክስ፣ ሣይኮሎጂ፣ እንግሊዝኛ፣ ብሔር /ብሔረሰብ ቋንቋ፣ ሂሣብ፣ የአካባቢ ሳይንስ፣ የጤናና ሰውነት ማጐልመሻ፣ ሲቪክስ ወዘተ…

### 1.6.2.1. ቋንቋዎች

ቋንቋ ለግንኙነትና ለትምህርት መስጫ ያገለግላል፡፡

▪ በት/ቤት ተማሪዎች ሊማሩዋቸው የሚገቡ ቋንቋዎች

***ሀ/ <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ</u>***

- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል፡፡
- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት /1-8/ በማስተማሪያነት ያገለግላል፡፡

***ለ/ <u>አገር አቀፍ ቋንቋ</u>***

- አገር አቀፍ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን በአገር ውስጥ ሁሉንም ብሔረሰብ የሚያገናኝ ነው፡፡
- አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑ፣ አማርኛ 1ኛ - 8ኛ ክፍል የትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል፡፡በአዲስ አበባ ከተማ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱ በአማርኛ ይሰጣል፡፡

***ሐ/ <u>ዓለም አቀፍ ቋንቋ፣</u>***

ከዓለም ጋር ለመግባቢያ የሚያገለግል ቋንቋ እንግሊዝኛ ሲሆን፣

- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል፡፡

#### 1.6.2.2. የሂሣብ ትምህርትና የተቀናጀ ሣይንስ ትምህርት

- ከ1-8 ላሉ ክፍሎች ለተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ከሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ከፍተኛ ክ/ጊዜያት ተመድቦላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ከ1ኛ-8ኛ ክፍሎች ከላይ በ1.6.2.1 እና በ1.6.2.2 ተ.ቁ. በተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ከሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ከፍተኛ ክፍለ ጊዜ መመደቡ ትኩረትን የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪ መምህራን፡-
  - በዕቅድ ላይ ተመስርተው በየጊዜው የተማሪዎችን ሥራ የመገመገም፣
  - ከግምገማው ውጤት በመነሳት የመማር ማስተማሩን ሂደት የማሻሻል፣
  - ደከም ያሉትን እና ልዩ ተሰጥዎ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት አስፈላጊውን ተጨማሪ ድጋፍ የመስጠት፣
  - የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም የማጠናከር ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

### *1.6.3. የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በትምህርት ዓይነት*

- በፈረቃ ለሚያስተምሩ ት/ቤቶች (ካሉ)
  - ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል በቀን 6 ክፍለ ጊዜ ይኖሩታል፡፡
  - የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ ሆኖ በሳምንት 30 ክፍለ ጊዜያት ይኖሩታል፡፡
- ሙሉ ቀን ለሚያስተምሩ ት/ቤቶች
  - ከ1ኛ -2ኛ ክፍል በቀን 6 ክፍለ ጊዜት ይኖራሉ።
  - ከ3ኛ ክፍልና ከዚያ በላይ 7 ክፍለ ጊዜያት ይኖራሉ።
  - የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 45 ደቂቃ ሆኖ በሳምንት 35 ክፍለ ጊዜያት ይኖሩታል፡፡

***<u>የመጀመሪያ ሳይክል በትምህርት አይነትና በክፍል ደረጃ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት፣</u>***

| ተራ ቁ. | የትምህርት ዓይነት | የሳምንቱ ክፍለ ጊዜ ሥርጭት በክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | አማርኛ | - | - | 3 | 3 |
| 2 | የሥነ ውበትና የሰውነት ማጐልመሻ | 6 | 6 | 4 | 4 |
| 3 | እንግሊዝኛ | 6 | 6 | 5 | 5 |
| 4 | የአካባቢ ሳይንስ | 7 | 7 | 7 | 7 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ሒሳብ | 6 | 6 | 6 | 6 |
| 6 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 5 | 5 | 5 | 5 |
| | ድ ም ር | 30 | 30 | 30 | 30 |

**የሁለተኛ ሳይክል /5-8/ በትምህርት አይነትና በክፍል ደረጃ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት፣**

| ተራ ቁ. | የትምህርት ዓይነት | የሳምንቱ ክፍለ ጊዜ ሥርጭት በክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ |
| 1 | አማርኛ | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 2 | ባዮሎጂ | - | - | 2 | 2 |
| 3 | ኬሚስትሪ | - | - | 2 | 2 |
| 4 | የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 5 | እንግሊዝኛ | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 6 | የተቀናጀ ሳይንስ | 4 | 4 | - | - |
| 7 | ሂሣብ | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 8 | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 9 | ስዕልና ሙዚቃ | 2 | 2 | 1 | 1 |
| 10 | የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 11 | ፊዚክስ | - | - | 3 | 3 |
| 12 | የህብረተሰብ ሳይንስ | 3 | 3 | 3 | 3 |
| | ድ ም ር | 30 | 30 | 30 | 30 |

***ማሳሰቢያ፡-***

*ከላይ በሰንጠረዡ የተጠቀሰው የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በቀጣይ ከ30 ክ/ጊዜ ወደ 35 ከፍ ሊል ይችላል፡፡ ይኸውም 5ቱ ክፍለ ጊዜ,የትና ለ5ኛ እና 6ኛ ክፍል በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በሒሳብና በጤናና የሰውነት ማጐልመሻና በተቀናጀ ሳይንስ ላይ አንዳንድ ክፍለ ጊዜ ይጨምራል፡፡ ለ7ኛና 8ኛ ክፍሎች ለአማርኛ 1 ክ/ጊዜ፣ ለሦስቱ የሣይንስ ትምህርቶች 3 ክ/ጊዜ፣ ለጤናና የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት 1 ክፍለ ጊዜ ይጨምራል፡፡*

### *1.6.4. የትምህርት ቤት አመራር አካላትና ሚናቸው (School management role)*

በት/ቤቶች ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ሚና ከሚጫወቱ አካላት መካከል ተገቢውን የማስተባበር እና የመምራትን ሥራ የሚያከናውን የትምህርት አመራር በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡

የት/ቤት አመራር አካላት ሲባል ር/መምህራን፣ መምህራንና የአካባቢውን ህብረተሰብና ወላጆች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የትምህርት ባለሙያዎችና ኃላፊዎችን ያጠቃልላል፡፡
የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በትምህርትና ሥልጠና እና አመራር ቦርድ ይመራሉ። ቦርዱ ከህ/ሰቡ፣ ከት/ቤቱ ማኅበረሰብና ከቀበሌ መስተዳድር የተውጣጡ አባላት ሲኖሩት አባላቱ በመልካም ስነ ምግባራቸው የተመሠከረላቸው እና በአመራር ችሎታቸው የተመሰገኑ ሆነው የቦርዱ ሰብሳቢ ከቀበሌ መስተዳድር የሚወከል ሲሆን የት/ቤቱ ር/መምህር የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።

እነዚህ አካላት በትምህርት ሥራ ላይ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ት/ቤቶች ህብረተሰቡን በማስተባበር በመማር ማስተማር ሥራ ላይ በባለቤትነት የሚሳተፉበትን ዕቅድ በማቀድና ለተግባራዊነቱም ያላስለሰ ጥረት በማድረግ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት፣
- የት/ቤቱን ማህበረሰብና የአካባቢው ህብረተሰብ በአጠቃላይ በውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ በማሳተፍ በተማሪዎች ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፣
- መምህራን በአመራር ሥራዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ቁልፍ በሆነ የውሣኔ አሰጣጥ ላይ ኃላፊነትን በማካፈል የባለቤትነት ስሜት ኖሮአቸው ሥራቸውን ብቃት እንዲወጡ ማስቻል፣
- መምህራን፣ የወላጅ ኮሚቴዎችና የትምህርት ባለሙያዎች በት/ቤት እቅድ ዝግጅትና አተገባበር ግምገማ ሂደቶች ላይ እንዲሣተፉ በማድረግ የት/ቤቱን ዕቀድ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣
- መምህራን በሥራቸው የበለጠ እንዲተጉ /እንዲበረቱ/ ባሳዩት ውጤት አርአያ የሆኑትን ለብቻ ስማቸውን በማስታወቂያ ሰሌዳ በይፋ በመለጠፍ እንዲታወቁና የማበረታቻ ሽልማት እንዲያገኙ በማድረግ፣

- ት/ቤቱ የተማሪዎችን ወላጆች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በመጥራት በልዩ ልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በት/ቤቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራዋቸው ማድረግ፣
- በት/ቤቱ ያጋጠሙ ችግሮችን በየጊዜው ለይቶ በማውጣት ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አስፈላጊ የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ችግሮቹን ማስወገድ፣
- ት/ቤትን ማዕከል ያደረገ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ መምህራን የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በትምህርቱ ዙርያ የሚታዩትን ችግሮች እንዲቀረፉና መምህራን ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ፣ በተጓዳኝ ትምህርት ጥሩ ተሳትፎ ያላቸው እና በጥሩ ሥነ-ምግባር ለሌሎች አርአያ የሆኑትን ተማሪዎች በማስታወቂያ ሰሌዳ ስም ዝርዝራቸውን በመለጠፍ እና ሽልማት በመስጠት በት/ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ እንዲታወቁ በማድረግ እና በሌሎች ተማሪዎች ዘንድም የተወዳዳሪነትን መንፈስ በማሳደግ ለበለጠ ውጤት እንዲነሳሱ ማስቻል፣
- በት/ቤት ውስጥ ካሉት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል በሥራቸው የላቀ ውጤት ያመጡትን የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ ማድረግ፣
- ከመምህራንና ተማሪዎች ጋር ሥራንና የትምህርት ውጤትን በማሻሻል ዙሪያ በየጊዜው ግልፅ ውይይት በማካሄድ የተሻለ የሥራ አፈጻጸም እንዲኖርና የተማሪዎች የትምህርት ውጤት እንዲሻሻል ማስቻል፣
- የአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማረጋገጫ ፖኬጅ መርሀ ግብሮችን ጠንቅቆ በማወቅና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም እንዲገነዘቡት በማድረግ የትምህርቱ ጥራት እንዲረጋገጥ ማስቻል፣
- የት/ቤቱን የውስጥ ለውስጥና ከሌሎች አቻ ት/ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ በማካሄድ የተሻለ አሠራርና ውጤት ማስመዝገብ፣
- የት/ቤቱን መምህራንና ሠራተኞች የሥልጠና ፍላጐት በመለየት ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማስቻል፣
- የት/ቤቱን የውስጥ ሱፐርቪዥን በማካሄድና በተገኘው ውጤት መሠረት መምህራን እርስ በእርስ እንዲማማሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተሻለ የሥራ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ፣

### *1.6.5. የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም*

- ትምህርት በሙሉ ቀን ይሰጣል፡፡
- በአሃዳዊ ክፍል /1-4/ በቀን 6 ክ/ጊዜ በሣምንት 30 ጊዜ ይሰጣል፡፡
- በመጀመሪያው ሳይክል /1-4/ ለ4 መማሪያ ክፍሎች አንድ ረዳት መምህር ይመደባል፡፡
- ረዳት መምህሩ በመደበኛነት የተመደቡ መምህራን በልዩ ልዩ ምክንያት ከሥራ ገበታቸው ሲቀሩ እነሱን በመተካት ማስተማርና በሌላም ጊዜ የቤት ሥራ በማረም የትም/ መርጃ መሣሪዎችን በማዘጋጀት በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች ድጋፍ በመሰጠትና በተጓዳኝ ትምህርት በመሣተፍ ተመድቦ ይሰራል፡፡
- አሃዳዊ ትምህርት የሚሰጠው ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሲሆን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡
    - አንድን ትምህርት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማዛመድ ለማስተማር ይረዳል፡፡
    - የተማሪውን ደካማና ጠንካራ ጐኖችን በመለየት እርዳታ ለመስጠት ያስችላል፡፡
    - የትምህርቱን አሰጣጥ እንደ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ለይቶ ለማቅረብ ይረዳል፡፡
    - መምህራን ለተማሪዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡
    - በሣምንቱ ውስጥ ሊሰጥ የሚገባው ክ/ጊዜ ሳይጓደል ፕሮግራሙን እንደአመቺነቱ ተለዋዋጭ ለማድረግ ያስችላል፡፡
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በቀን 6 ክፍለ ጊዜ በሳምንት 30 ክፍለ ጊዜ ይሰጣል፡፡
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ከክፍል ወደ ክፍል በመዘዋወር ትምህርቱን ይሰጣሉ፡፡ መምህራኑ በሰለጠኑባቸው የትምህርት ዓይነቶች ይመደባሉ፡፡

#### 1.6.5.1. የመምህራን የሥራ ሰዓት አጠቃቀም

የአንድ መምህር የሳምንት መደበኛ የሥራ ሰዓት 40 ሰዓት ሆኖ ይህም ለትምህርት ዝግጅት፣ ክፍል ውስጥ ገብቶ ለማስተማር፣ የተማሪዎችን ሥራ ለማረምና ለመከታተል ይጠቀምበታል፡፡

- ክፍል ውስጥ ገብቶ ለማስተማር 22፡30 ሰዓት
- ለትምህርት ዝግጅትና የተማሪዎች ሥራ ለማረምና ለመከታተል 11፡30 ሰዓት
- ለተጓዳኝ ትምህርት 3 ሰዓት
- ለልዩ ልዩ ሥራዎች እስከ 3 ሰዓት ይሆናል፡፡

- የተጠቀሰው የሥራ ሰዓት እንደወቅቱ የሥራ ሁኔታ አመቺነት ተከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- የአንድ መምህር የክፍለ ጊዜ ብዛት ከሚፈለገው በታች ከሆነ አንደአስፈላጊነቱ በተመሣሣይ የትምህርት ዓይነትም ሆነ በሌላ ሥራ ላይ ተመድቦ/ተመድባ ይሰራል/ትሰራለች፡፡
- ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ባለው ደረጃ የሚየስተምሩ መምህራን በክላስተር ሞዳሊቲ የሰለጠኑ ሆነው በሰለጠኑባቸው  የትምህርት ዓይነቶች ያስተምራሉ፡፡
- ከ5ኛ - 8ኛ ባሉ ክፍሎች አንድ መምህር ብዙ ሴክሽኖች ባሉበት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይንም በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተመድቦ/ተመድባ ያስተምራል/ ታስተምራለች፡፡

### 1.6.5.2. ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ

መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ቀዳሚ ሥፍራ ስላላቸው  ያለእነሱ ብርቱ ጥረት ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት አይታሰብም፡፡

መምህራን በማስተማር ችሎታቸው የሚተማመኑ ለተማሪዎችና ለሥራቸው ጥንቃቄ የሚያደርጉና እርስ በርሳቸው የሚረዳዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መምህራን በማስተማሩ ረገድ ተጨባጭ እቅድ በማዘጋጀት ከሁሉም አስቀድመው ሙያዊ ግዴታቸውን ለመወጣት እንዲችሉ የሚከተሉት ቁልፍ ሚናዎች ይኖራቸዋል።

- መምህሩ በክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አዋኪ-የሆኑት /ሲጋራ ማጨስ፣ሞባይል መጠቀም፣ወ.ዘ.ተ ከማድረግ መቆጠብ፣
- የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘትና አቀራረብን ጠንቅቆ በማወቅ፣ተማሪዎች ከነበሩበት ደረጃ ወደ ተሻለ ውጤት ማብቃት፣

- ግልጽ የሆነ ግብ በመንደፍ ለተግባራዊነቱ ያላሰለሰ ጥረት በማካሄድ፣ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ፣
- የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪው በሚያመች ግልጽ፣ ሳቢ፣ ማራኪ እና አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ (Active Learning) በመጠቀም ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ፣
- ለት/ቤቱ ንብረቶች ከፍተኛ እንክብካቤ በማድረግ ተገቢ ግልጋሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ውጤታማ የሆነ የክፍል አያያዝ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ፣
- ለተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር መሻሻል በማቀድና በመተግበር ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት /መከራረጅ፣ መደባደብ፣ የት/ቤት ንብረት ማውደም ወ.ዘ.ተ/
- ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በሚገባ ለመረዳታቸው በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንደተማሪው የትምህርት አቀባበል የባህሪ ለውጥ ማምጣት፣
- ተከታታይ ግምገማና ምዘና በማካሄድ በተገኘው ውጤት መሠረት የማስተማር ዘዴዎችን ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበል አኳያ በመጠቀም ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት ማብቃት ፣
- በት/ቤቱ ማህበረሰብም ሆነ በሌላ የመልካም ሥነ ምግባር አርአያ ሆኖ መገኘት፣
- በተማሪዎች መካከል የፆታ እኩልነትና የችሎታ ልዩነት መኖሩን በመረዳት እና ተገቢ ድጋፍ በመስጠት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት፣
- ሙያቸውን ለማሻሻል እርስ በርሳቸው የሚማማሩባቸውና ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጣጡባቸውን መድረኮችን በመፍጠር አቅምን - ማዳበር፣
- በት/ቤቱ የሥራ ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ በመሣተፍና ከወላጆችና ከተማሪዎች ጋር በመወያየት በመማር ማስተማር ሥራ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፣
- የት/ቤቱን የደምብ ልብስ /ጋዋን/ መልበስና ማንነታቸውን የሚገልፅ ባጅ ማድረግ።

### 1.6.6. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም

- አብዛኛዎቹ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ይዘቶች ከመደበኛ ትምህርት ይዘቶች ጋር ተቀናጅተውና ተዋህደው ስለሚሰጡ የተለየ የክ/ጊዜ ስርጭት አያስፈልጋቸውም፡፡

- የተለየ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መምህሩ አመቺ የሆነ ክፍለ ጊዜ በመስጠት ለእያንዳንዱ ተማሪ ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
- አንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር የሥራ ሰዓት ከመደበኛው ት/ቤት መምህር እኩል ነው፡፡

### 1.6.6.1. የአእምሮ ውስንነት ላላቸው /1-4/

- ለመደበኛው የትምህርት ፕሮግራምና ለእድገት ዘርፎች የሚረዱ ስልጠናዎች ማለትም በቋንቋ፣ በንባብና ቅድመ ንባብ፣ በቁጥር፣ በማህበራዊ እድገት፣ በሥነ ስዕል፣ በእጅሥራና በድራማ ትምህርቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡

### 1.6.6.2. ማየት ለተሳናቸው /1-4/

- የስሜት ህዋሳት ስልጠና፣ ነፃ እንቅስቃሴና ትውውቅ፣ የአባካስ፣ የብሬል ንባብና ጽሕፈት፣ ጽሑፍን በቴፕ አቀራረጽ፣ መተየብ፣ የእጅ ጽሕፈትና የዕለት ተዕለት ክሂል ካዳበሩ በኋላ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመቀላቀል ይማራሉ፡፡

### 1.6.6.3. መስማት ለተሳናቸው /1-8/

መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የነፍስ ወከፍና የቡድን ንግግር፣ የማዳመጥ ሥልጠናና የቋንቋ ችሎታን ማዳበር የመሣሠሉ ክሂሎችን ይማራሉ፡፡

### 1.6.6.4. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል

የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራን ድልድል እንደ መደበኛው ት/ቤት የመምህራንና ሠራተኞች ድልድል ሆኖ፣ በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ10-20 ለሚሆኑት የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ልዩ ክፍልና ተጨማሪ የሰው ኃይል እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- የማየት ጉድለት ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ ልዩ መምህር፣
- የመስማት ጉድለት ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ መምህር፣
- የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ ረዳት መምህር ወይም ሞግዚት፣
- የስሜት መረበሽ ላጋጠማቸው አንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር፣ አንድ የሳይኮሎጂ ባለሙያ፣
- የመማር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ ረዳት መምህር፣
- የአንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር የሥራ ሰዓት ከመደበኛው ትምህርት መምህር እኩል ነው፡፡
- የመናገር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ የአንደበት ወጌሻ፣

- የአካል ጉድለት ላለባቸው አንድ ረዳት መምህር ወይም ሞግዚት፣
- ተደራራቢ ችግር ላለባቸው እንደየሁኔታው ታይቶ የሰው ኃይል ይመደባል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሕፃን የመስማትና የማየት ጭምር ችግር ካለበት የሰው ኃይል ምደባው አንድ ባለሙያ ለአንድ ወይም ለሁለት ሕፃናት ይሆናል፡፡
- ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ሕፃናት የሚመደበው ባለሙያ እንደየሕፃናቱ አእምሮ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ ሁኔታ ይለያያል፡፡ <u>**ለምሳሌ**</u> አንድ ሕፃን በሂሣብ ትምህርት ወይም በሥዕል ወዘተ. ከሌሎች ሕፃናት በጣም የመጠቀ ችሎታ ካለው በዚህ ትምህርት እንዲገፋበት የሚመለከተውና ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦለት እንዲከታተለውና እንዲያበረታታው ይደረጋል፡፡

ልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናትና ወጣቶች ከሌሎች መደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ በሚደረግበት ጊዜ የተለየ ክህሎትና ይዘት እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲቻል ከመደበኛ ክፍሎችና የትምህርት ጊዜ ውጭ በልዩ ክፍሎች (unit) በልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራንና ባለሙያዎች ይስተናገዳሉ፡፡

### *1.6.7. የሙሉ ቀን ትምህርት*

የተማሪዎች ብዛት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ በመምጣቱ ት/ቤቶች እነዚህን ተማሪዎች ተቀብለው ለማስተናገድ ባለመቻላቸው ምክንያት ትምህርት በሁለት ፈረቃዎች እንዲሰጥ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ አሠራር ለጊዜው ለችግር ማቃለያነት ተብሎ የተወሰደ ቢሆንም ተማሪው በቀን ውስጥ ማግኘት የሚገባውን ትምህርት በስፋትና በጥልቀት እንዲያገኝ ስለማያስችለው በትምህርቱ ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ በሁለት ፈረቃ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ቀስ በቀስ ሁኔታውን በማመቻቸት ሙሉ ቀን እንዲያስተምሩ ይደረጋል፡፡ ከአሁን በኋላ የሚከፈቱ ት/ቤቶች ግን ትምህርት የሚሰጡት በሙሉ ቀን ፕሮግራም ይሆናል፡፡ የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ ከክፍል ውጭ ይሰጣል፡፡

### *1.6.8. የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም*

የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ትምህርት ውጭ የመማር ማስተማር ሥራ ለማገዝ የሚሰጥ ትምህርት ሆኖ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡ ተማሪው የበለጠ እውቀት እንዲገበይ ለመርዳት፣

- ተማሪው ለሙያ ሥራ አክብሮትና ጥሩ አመለካከት እንዲኖረው ለማድረግ፣

- ተማሪዎች ዕምቅ ችሎታቸውን በማውጣትና በማዳበር በፍላጎታቸውና የሙያ መስክ ለመምረጥ እንዲችሉ ዕድል ለመስጠት፣
- ችሎታቸውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት እንዲያዳብሩ፣
- የሥራ ፍላጎትና ፍቅር ለመፍጠርና ለማዳበር፣
- ተማሪዎች ማህበራዊ ግልጋሎቶችን እንዲሰጡ ለማበረታታት፣
- በክፍል ውስጥ በሚሰጡ ትምህርቶች ሊገኙ የማይችሉ የማቀድ፣ የመምራት፣ የማስተባበርና የመገምገም፣ ኃላፊነትን የመቀበል ውሳኔ የመስጠትን ችግሮችን በራስ ተነሳሽነትና በፈጠራ የመፍታትን ክህሎቶችንና ልምዶችን ለማዳበር፣
- ትርፍ ጊዜያቸውን ትምህርት በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲያሳልፉ ለማድረግ፣ ተጨማሪ ደስታና ልዩ ስሜት ለመፍጠር፣
- በጥልቀትና በስፋት እንዲሰጡ የሚደረጉ የትምህርት ዓይነቶች አማካይነት ለሚደክሙ ተማሪዎች ልዩ እርዳታ ለመስጠት፣
- አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮችን፣ አዳዲስ ክስተቶችንና ግኝቶችን ለተማሪዎች ለማስተዋወቅና ብሎም በመፍትሄ ሰጪነት ለማሳተፍ፣

የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም በትምህርት ቤቱ አቅምና እቅድ መሠረት የተለያዩ ክበባትንና ቡድኖችን በማቋቋም በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርቶች በእያንዳንዱ ተማሪ ዝንባሌ፣ ፍላጎትና ችሎታ መሠረት ያደረገ እውቀትንና ክህሎትን ያዳብራል፡፡

የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም የሚከናወነው መደበኛውን የትምህርት ጊዜ ሳይሻማ አንዳንድ ሥራዎችን ለመስራት ያስችላል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ጊዜያቸውን እንደፍላጎታቸው አራዝመውና አሳጥረው እንዲሰሩ ይረዳቸዋል፡፡ ፕሮግራሙ እንደተማሪው ዕድሜና ጥንካሬ በሳምንት ከ4 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል፡፡

### *1.6.9. የመማር ማስተማር መመሪያዎች*

#### 1.6.9.1. አጠቃላይ መመሪያዎች፣

- ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- የየትምህርቱ ዓይነት መርሀ ትምህርቶች፣
- የመምህሩ መምሪያዎችና መርጃ መጻሕፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የተማሪው መጽሐፍ በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የትምህርት ካሌንደር፡፡

#### 1.6.9.2. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መመሪያዎች

- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪም
  - ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለባቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - የልዩ ፍላጐት ትምህርት መርሃግብር እስትራቴጅ፣

#### 1.6.9.3. ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች

- የአጠቃላይ ትምህርት አመራር አደረጃጀት የህብረተሰብ ተሳትፎ የፋይናንስ መመሪያ (Blue Book)፣
- የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር መመሪያ፣
- አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ፣
- የአርብቶ አደር እስትራተጂ፣
- ስለግል የትምህርት ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብና ማብራሪያ /ለግል ት/ቤቶች/፣
- አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት፣
- የማዕከልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 41/85፣
- የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል መመሪያ /ቀድሞ የተዘጋጀው/፣
- የት/ቤቶች ተጨማሪ በጀት መመሪያ (School grant manual)፣
- አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት እስትራተጂ፣
- የመምህራን ልማት ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የት/ቤት መሻሻል ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣
- የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት ፕሮግራም መመሪያዎች፣
- የትምህርት ሕግ።

### 1.7. የማስተማር ዘዴ /Teaching Methodology/

በት/ቤቶች ካሉት ችግሮች መካከል በዋናነት በርካታ ተማሪዎች በትምህርታቸው በሚፈለገው መጠን ውጤታማ ሆነው አለመገኘት ነው፡፡ ለዚህ ምክንያት ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት ውስጥ፡-

- ተማሪዎች፣ ወላጅና ት/ቤት በሚፈለገው መጠን በትምህርቱ ሥራ በቅንጅት አለመሳተፍና
- የትምህርቱ አሰጣጥ ማራኪና ሳቢ ባለመሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ አዘወትሮ መቅረትና ማቋረጥ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡

ይህን ችግር ለመቅረፍ ት/ቤቶች፣ ወላጅ፣ የአካባቢው ህብረተሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ በመወያየት ተማሪዎችን ሊያበረታታና ሊያሳትፍ የሚችል ትርጉም ያለው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሊቀይሱ ይገባል፡፡ ስለመምህራን የጊዜ ሰሌዳና የሪሶርስን አጠቃቀም በተመለከተ **ለተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ** ተግባራዊነት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪ ተኮር እና ብቃትን መሠረት ያደረገ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ይከተላሉ፡፡ ይህም እው ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ማድረግ ሲቻል ነው።

  - የት/ቤቱ ቀዳሚ ዓላማና ተግባር የተማሪዎችን ፍላጐት ሚሟላት ላይ ማተኮር፣
  - ለሁለም ተማሪዎች ስኬታማነት /ውጤታማነት/ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
  - በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ዲሞክራሲያዊ የሆነ ግንኙነትን በማጠናከር ተማሪዎች ካለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ማድረግ፣
  - የመማር፣ የትምህርት መሻሻል፣ የትምህርት አኩልነት፣ የትምህርት ፍትሃዊነትና መከባበር የት/ቤት ባህል ማድረግ፣

* እንደአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶች የተማሪዎችን የግልና፣ የቡድን ችሎታ፣ ፍላጐት፣ ዕድሜ፣ የመማር ዘይቤና ቀዳሚ ተሞክሮ ላይ የተመሠረተ የትምህርት አቀራረብና የምዘና ሥርዓት ሊከተሉ ይገባል፡፡

## 1.8. የትምህርት ምዘናና የማለፊያ ነጥብ

የአገራችን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ትኩረት ከሰጣቸው ክፍሎች አንዱ የትምህርት ምዘና ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው የሚሰጠውን ትምህርት በተሟላ ሁኔታ በመማር የባህሪ ለውጥ ለማሳየታቸው የመማር ማስተማሩን ክንውን ለማሻሻልና የትምህርት ተግባር በጥራት መካሄዱን ለማረጋገጥ የትምህርት ምዘና

ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በአጠቃላይ የትምህርት ምዘና የትምህርት ሂደት አካል እንደመሆኑ መጠን በጥራት መለኪያነትም የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡

ተማሪዎች ተገቢውን እውቀትና ክህሎት መጨበጣቸውን እንዲሁም መምህራን በአግባቡ ማስተማራቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ በመምህራን የሚካሄደው ተከታታይ ምዘና (Continuous Assessment) ዋነኛውና እጅግ አሰፈላጊ የትምህርት ምዘና አካል ነው፡፡

ስለሆነም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከ1ኛ-3ኛ ባሉት ክፍሎች የተከታታይ ምዘና ስልት ሆኖ ነፃ የክፍል ክፍል ዝውውር ይደረጋል፡፡

- ከ4ኛ-7ኛ ክፍሎች ከተከታታይ ምዘና በተጨማሪ የማጠቃለያ ግምገማ በማካሄድ ወደሚቀጥለው ክፍል የሚዘዋወሩት በየደረጃው በተቀመጠው የምዘና ሥልት መሠረት ሆኖ መንግሥት ለት/ቤቶች በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
- ከ4ኛ-7ኛ ክፍሎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ማለፍ ላልቻሉ ተማሪዎች የክልሉ ትምህርት ቢሮ ክፍል መድገምን በሚመለከት ለትምህርት ተቋማት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
- ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል ለመዛወር ፈተናውንም ሆነ የማለፍያ ነጥብ ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡

## 1.9. የተማሪዎች ሚና (students' role)

በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ለውጥ ሊመጣ ከሚችልባቸው ዋነኛ ጉዳዮች መካከል የተማሪዎች የራሳቸው ጥረት አንዱ ሲሆን ተማሪዎች በጥሩ ዲስፕሊን ታንፀው የትምህርት ቤትን ደንብና ሥነ-ሥርዓት በማክበር ትምህርታቸውን በንቃት የመከታተልና ለጥሩ ውጤት በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከመምህሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ መምህሩ የሚሰጠውን ትምህርት በጥሞና መከታተል፣ ከት/ቤት ያለበቂ ምክንያት ያለመቅረት፣ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን እንዲሁም የችሎታ መመዘኛዎችን ሠርተውና አጠናቀው በጊዜ ማቅረብ፣
- የት/ቤቱ አመራር አካላት የሚሰጡትን ምክር፣ ድጋፍና መመሪያ በአግባቡ በመፈፀም በዲስፕሊን የታነፀ ሆኖ መገኘትና ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት በት/ቤቱ ውስጥ እንዲኖር አስተዋፅኦ ማድረግ፣

- የት/ቤቱን የደምብ ልብስ መልበስና በአጠቃላይ ሥነ-ሥርዓትን የተከተለ አለባበስ (በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያለው አለባበስ) የሚለብሱ፣ አካላዊ ንጽህናቸውን የጠበቁና በሌሎች ጓደኞቻቸው ዘንድም በመልካም አርአያነት የሚጠቀሱ ሆኖ መገኘት፣
- በቡድን በመስራት እርስ በርስ በመረዳዳትና በመማማር በጋራ የመሥራትን፣ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን እና የመቻቻል ባህልን ማዳበር፣
- በተለያዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ውስጥ በመሣተፍ እውቀትና ክህሎት የመቅሰም ፍላጐትና ችሎታ የላቸው መሆን፣
- የሀገሪቱን ህገ መንግሥት ጠንቅቆ በማወቅ በት/ቤት ግቢም ሆነ ውጭ መብታቸውን ማስከበርና ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት፣
- ለት/ቤቱ ማህበረሰብ አክብሮት ያላቸውና ት/ቤቱን የሚወዱ በዚህም የተነሣ ትርፍ ጊዜያቸውን በት/ቤቱ ውስጥ የቲቶሪያልና የማካካሻ ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የተሻለ ውጤት ማምጣት፣
- በቤተሙከራዎች ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሆነው በቤተመጽሓፍት አዘወትረው በመጠቀም ተግባራዊና ንድፈ ሀሳባዊ ዕውቀትን ማዳበር፣
- የመጠየቅ፣ የመመራመርና የማወቅ ፍላጐታቸው ከፍተኛ የሆነና በራስ የመተማመን ብቃት ለማዳበር የሚተጉ፣
- የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያደናቅፉ ነገሮች /ሞባይል መጠቀም፣አልኮል ጠጥቶ ክፍል መግባት ወዘተ/ መቆጠብ።

## 1.10. የወላጆች ሚና (parents role)

ወላጆች ከት/ቤት ሥራ ጋር የተያያዙ የመማርና የማስተማር ሂደትን የሚያጐልብቱ የተለያዩ ግልጋሎቶችን መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወላጆች የልጆቻቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታና የሀገራቸውን እድገት ሊሳካ የሚችለው የችግሮች ሁሉ መፍቻ በሆነው በትምህርት ሥራ በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ መሆኑ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ ወላጆች የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ለት/ቤቶች አስፈላጊ የገንዘብ ድጋፍና የትምህርት ቁሳቁሶችን በማሟላት ት/ቤቶችን ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከት/ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር በት/ቤቶች አመራር ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት፣

- የተማሩ ወላጆች በት/ቤት በመገኘት ቲቶሪያል በመስጠትና በሌሎች ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ፣
- ለልጆቻቸው ለትምህርት የሚያስፈልጓአቸውን የትምህርት ቁሳቁሶች ማሟላት፣
- በተለያዩ ጊዜያት ት/ቤት ድረስ በመምጣት ስለልጆቻቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ ማስቻል፣
- ልጆቻቸው የቤት ሥራ ለመሥራትም ሆነ ለጥናት ምቹ አካባቢና የጥናት ጊዜ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው አዘወትረው መገኘታቸውንና የት/ቤቱን ህግና ሥነ- ሥርዓት መጠበቃቸውን ከት/ቤቱ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ጥረት ማድረግ፣

## 1.11. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ የሚገባው

በት/ቤቶችና በህብረተሰቡ መካከል ጥብቅ ትሥሥር ሊኖር ይገባል። ት/ቤቶች ራሳቸውን እንደ ደሴት ሳይቆጥሩ ህብረተሰቡን በትምህርቱ ሥራ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህም፡-

- ወላጆች አቅም በፈቀደ መጠን ለልጆቻቸው የተመጣጠነ ምግብ፣ በቂ የጥናት ስፍራና የእረፍት ጊዜ እንዲሰጡአቸው ማበረታታት፣
- ልጆች የቤት ሥራና ሌሎች ከትምህርት ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ሲሰጡአቸው ወላጆች እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ለወላጆች በመደበኛነት ስለልጆቻቸው የትምህርት አቀባበልና ክትትል ምክር በመስጠት የልጆቻቸው የትምህርት ውጤት እንዲሻሻል አቅዶ መንቀሳቀስና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በተማሪ ውጤትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ፎርም በማዘጋጀት ለወላጅ በየጊዜው የሚያሳውቁበት መንገድ በማቀድ ሥራ ላይ ማዋል፣
- በት/ቤት በኩል የሚወጡ ማስታወቂያዎች ለወላጆች ግልጽና በቀላሉ ሊረዱዋቸው በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ መተግበር፣
- በት/ቤት እቅድ ዝግጅት ወላጆች ከመምህራን ጋር ተሳትፎ እንዲኖራቸው መጋበዝ፣

- የወላጆች ልማን የሆኑ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ለወላጆች እንዲደርሱ ማድረግ፣
- የወላጆችና የት/ቤት ግንኙነት ለማጠናከር ወላጆችን ያሣተፉ ትምህርታዊ መዝናኛ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣
- በወላጆች ቀን ወላጆች ት/ቤት በመገኘት የት/ቤቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤት አውቀው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አቅዶ ተግባራዊ ማድረግ፣

## 1.12. በትምህርት ሥራ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ

ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቶችን በማሻሻል፣ በመገንባት፣ የውስጥ ገቢን በማሳደግ፣ በትምህርት አመራርና በሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ በባለቤትነት ስሜት በመሳተፍ የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ጉልህ ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡ ይህም፡-

- ት/ቤት ሲቋቋም ማህበረሰቡ የሚፈልገውን ጥቅም እንዲሰጥ ሆኖ መደራጀቱን ያረጋግጣል፡፡
- ለት/ቤቶች መሻሻል ባለው አቅም የገንዘብ ድጋፍና የትምህርት ቁሳቁሶች ያሟላል፡፡
- በት/ቤቶች በተለያየ የአመራር ደረጃ በመሳተፍ ላይ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡
- የተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በት/ቤቶች በመገኘት በቲቶሪያልና በሌሎች የትምህርት እንቅስቃሴዎች ላይ  ድጋፍ በማድረግ የትምህርቱን ጥራት ከፍ እንዲል የራሳቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡
- ለችግረኞችና ለወላጅ አልባ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ከትምህርታቸው እንዳይተጓጐሉ ጥረት ያደርጋል፡፡
- ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር ዕድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ት/ቤት እንዲመጡና ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።
- በተለያዩ የትምህርት ኮሚቴዎች በመወከል ከእቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ትግበራ ሂደት ላይ በመሳተፍና አፈፃፀሙንም በመከታተልና በመቆጣጠር የትምህርቱ ሥራ በአግባቡ እንዲካሄድ እገዛ ያደርጋል።
- በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ላይ ተሳትፎ በማድረግ ትምህርቱ ተገቢነትና ተጨባጭነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል ድርሻውን ይወጣል፡፡

## 1.13. ልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች

### *1.13.1. የሬዲዮ ትምህርት*

***<u>ሬደዮ ለመደበኛ ትምህርት ሂደት ያለው ጠቀሜታ</u>***

*የመደበኛ ትምህርት ሲባል ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ ተዘጋጅቶ ሕንፃው ተሰርቶ ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ተሟልተው፣ ሥርዓተ ትምህርት ተዋቅሮ፣ የመማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተው፣ መምህር ተቀጥሮ የጊዜ ሰሌዳው ወጥቶ በሙሉ ጊዜ የሚካሄድ የትምህርት ሂደት ነው፡፡*

*የአንድን አገር እድገት ለማፋጠን ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ትምህርት ነውና ትምህርቱ ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ በአቀባዩና በተቀባዩ መካከል ስኬታማ የሆነ ተግባቦት* (effective Communication) *ሲኖር ነው፡፡ ስለሆነም ተግባቦትና ትምህርት በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ መማር፣ ማወቅና የአስተሳሰብ አድማስን ማስፋት የተግባቦት ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ለመደበኛም ሆነ መደበኛ ላልሆነው ትምህርት ሬድዮ አማራጭ ያልተገኘለት መገናኛ መሣሪያ ነው፡፡*

*የሬዲዮ ትምህርት ከሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች የተመረጠበት ምክንያት፡-*

- *ወጪው አነስተኛ በመሆኑ፣*
- *ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ አመቺ በመሆኑ በተለይ ለገጠሩ ህብረተሰብ፣*
- *በአንድ በተወሰነ ሰዓት ብዙ ሰው ማስተማር ማስቻሉ፣*
- *የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እገዛ ማድረጉ፣*
- *የባለሙያዎችን እውቀትና ልምድ በቀላሉ ወደ ክፍል ተማሪዎች ማምጣት መቻሉ፣*
- *የጥቂት ብቁ መምህራንን የማስተማር ዘዴና ልምድ ለሌሎች ለማካፈል ማስቻሉ፣*
- *በየት/ተቋማት ውስጥ ያለውን የትም/ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች ችግር ማቃለሉ፣ ወዘተ... ናቸው፡፡*

***<u>የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮና ሥርዓተ ትምህርት ቅንጅት</u>***

*የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮ ፕሮግራም፣*

- *ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይዘጋጃል፣*
- *እንደ የሁኔታው በእያንዳንዱ የት/ዓይነት እየተዘጋጀ ይሠራጫል፣*
- *በአገሪቱ ሥ/ትምህርት መሠረት ይዘጋጃል።*

*ይህም በመሆኑ በትምህርት ሬዲዮና ሥርዓተ ትምህርት ዓላማዎች፣ ይዘቶች የአቀራረብ ዘዴዎችና ግምገማ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ሊኖር ይገባል፡፡*

## መደበኛ የሬዲዮ ትምህርት ሚና

የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮ ፕሮግራም በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተማሪዎችን ዓላማ ያደረጉ ሦስት ሚናዎች አሉት፡፡

1. በማጠናከሪያነት (enrichment)
2. በመማር መድብልነት (learning resources)
3. በቀጥታ በማስተማሪያነት (Bates, 1984)

**የሬዲዮ ትምህርት ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈለጉ ዝግጅቶች**

- የሬድዮ ትምህርት መቀበያ ሬድዮኖች፣
- የሬድዮ ማዕከላት ወይም የሬድዮ መማሪያ ክፍሎች፣ የመብራትና የስኬት እንስታሌሽን፣
- የሬድዮ ትምህርት የሥርጭት የጊዜ ሰሌዳ፣
- በእያንዳንዱ የት/ዓይነት የተዘጋጀ የሬድዮ የመምህሩ መምሪያ።

**ባለሙያዎችን በተመለከተ**

- ባለሙያዎቹ ከመምህራን ይመለመላሉ፣
- በሬድዮ ትምህርት ሥልጠና የወሰዱ መሆን ይኖርባቸዋል።

# የ2001 ዓ.ም የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት ፕሮግራም

## (ከለገዳዲ ትም/ማስራጫ ጣቢያ የተወሰደ)

| የክፍል ፔሬድ | የክፍል ፔሬድ ሰዓት ሙሉ ቀን | የሬዲዮ ሥርጭት ሰዓት | ሰኞ | | ማክሰኞ | | ረቡዕ | | ሐሙስ | | አርብ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የት/ዓይነት | ክፍል | የት/ዓይነት | ክፍል | የት/ዓይነት | ክፍል | የት/ዓይነት | ክፍል | የት/ዓይነት | ክፍል |
| 1 | 2:15 - 3:00 | 2:20 - 2:35 | እንግሊዝኛ | 3 | እንግሊዝኛ | 3 | እንግሊዝኛ | 3 | እንግሊዝኛ | 3 | እንግሊዝኛ | |
| 2 | 3:05 - 3:50 | 3:10 - 3:25 | እንግሊዝኛ | 1 | እንግሊዝኛ | 1 | እንግሊዝኛ | 1 | እንግሊዝኛ | 1 | አካባቢ ሳይንስ | |
| | | 3:55 - 3:50 | ሕብረት | 5 | ሣይንሰ | 5 | እንግሊዝኛ | 8 | አማርኛ | 6 | እንግሊዝኛ | |
| 3 | 3:55 - 4:40 | 4:00 - 4:15 | አማርኛ | 4 | አካባቢ ሳይንስ | 2 | አማርኛ | 1 | አካባቢ ሣይንስ | 3 | አማርኛ | |
| | 4:40 - 4:55 | እረፍት | እረፍት | | እረፍት | | እረፍት | | እረፍት | | እረፍት | |
| 4 | 5:00 - 5:45 | 5:30 - 5:45 | አማርኛ | 8 | አካባቢ ሳይንስ | 4 | አማርኛ | 8 | አማርኛ | 7 | ሳይንስ | |
| 5 | 5:50 - 6:35 | 6:15 - 6:30 | ሳይንሰ | 6 | ሕብረተሰብ | 5 | እንግሊዝኛ | 5 | አካባቢ ሳይንሰ | 1 | አካባቢ ሳይንስ | |
| 6 | 8:00 - 8:45 | 8:05 - 8:20 | እንግሊዝኛ | 4 | እንግሊዝኛ | 4 | እንግሊዝኛ | 4 | እንግሊዝኛ | 4 | አካባቢ ሳይንስ | |
| | | 8:25 - 8:40 | አካባቢ ሣይንሰ | 3 | ሐብረት | 6 | አማርኛ | 7 | ሳይንሰ | 6 | አማርኛ | |
| 7 | 8:50 - 9:35 | 8:55 - 9:10 | እንግሊዝኛ | 2 | እንግሊዝኛ | 2 | እንግሊኛ | 2 | እንግሊዝኛ | 2 | አማርኛ | |
| | 8:15 - 9:30 | 9:15 - 9:30 | ሕብረተሰብ | 6 | እንግሊዝኛ | 5 | እንግሊዝኛ | 6 | እንግሊዝኛ | 7 | እንግሊዝኛ | |

**ማሳሰቢያ፡-**

❖ የእንግሊዝኛ IRI ፕሮግራሞች ከሰኞ - ሐሙስ በየቀኑ አዳዲስ ፕሮግራሞች ስለሚሰራጩ ለእያንዳንዱ ክፍል ሁሉንም IRI ስርጭት ማስደመጥ ይገባል፡፡

- የ1ኛ መንፈቀ ዓመት የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት መስከረም 26/2001 ተጀምሮ በየሳምንቱ እየተካሄደ ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡
- የ2ኛ መንፈቀ ዓመት የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት የካቲት 16/2001 ተጀምሮ በየሳምንቱ እየተካሄደ ግንቦት 21/2001 ዓ.ም ያበቃል፡፡
- የዐውደ ዓመት /የሕዝብ በዓላት/ ዕለቶች የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት አይኖርም፡፡

ከላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ክልሎች እንደየአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቀቀማቸውና የጊዜ ሰሌዳቸው መሠረት በማጣጣም መጠቀም ይችላሉ፡፡

### 1.13.2. ቤተ ሙከራ

የመማር ማስተማር ሥራ ውጤታማ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ትምህርቱ በንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ ተወስኖ ከሚሰጥ ይልቅ በተግባር ተደግፎ ሲሰጥ እንደሆነ የትምህርት ባለሙያዎች አበክረው ያስረዳሉ፡፡ በተለይ እድሜአቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ይህ ጉዳይ የበለጠ ይመለከታቸዋል፡፡ ተማሪዎች ፈጣሪዎችና ተመራማሪዎች የሚሆኑት ዕለት በዕለት የሚሰጠውን ትምህርት ራሳቸው በተግባር ሲሞክሩትና ከውጤቱም መማር ሲችሉ ነው፡፡ በቤተ ሙከራ የሳይንስ መርጃ መሣሪያዎች መኖር ዓላማ የምልከታ፡ የመለካት፣ የመመራመር፣ የዲዛይን፣ ግንባታና አካባቢን የማጥናት ክሂሎችን ተማሪው እንዲያጐለብት ለማድረግ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ሊኖሩ የሚገቡ የሣይንስ መርጃ መሣሪያዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ቻርቶች /ሥዕሎች ፎቶግራፎች፣
- ሞዴሎች፣
- ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች/ቢከር፣ ፔትሪ ስሃን፣ ፍላስክ... አካላት፣
- የተሟሉ የሣይንስ ኪቶች፣
- ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ቅርሶች፣
- መገልገያ መሣሪያዎች፣
- መለኪያ መሣሪያዎች /ርዝመት፣ ግዝፈት፣ አንግል፣ ይዘት፣ ጊዜ/፣
- የእጅ መሣሪያዎች /መዶሻ፣ መጋዝ/፣
- የነበሩ ናሙናዎች (Preserved specimen)፣
- በአካባቢው የሚገኙ /ህይወት ያላቸውና የሌላቸው/ ነገሮች፣

### 1.13.3. የቤተመጻሕፍት አገልግሎት

#### ሀ/ <u>የቤተ መፃህፍት አደረጃጀት</u>

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መፃሕፍት የሚደራጀው በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ሆኖ ከተለያዩ አዋኪ ድምፆች የራቀና ለት/ቤቱ ህብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት በሚችል መልኩ መሆን አለበት፡፡

የቤተ መጻሕፍት በአንድ ት/ቤት መኖር ፋይዳው፡-

- ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና እንዲሁም ለአካባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ መጻሕፍትን በማቅረብ የንባብ ፍላጎትን ለማዳበር፣
- በተለያዩ የትምህርት ርዕሶች ዙሪያ ለሚካሄዱ ጥናቶች በምንጭነት ለማገልገል፣
- ተማሪዎች ትርፍ ጊዜአቸውን በቤተመፃሕፍት መጻሕፍት በማንበብና እንዲያሳልፉ ለማድረግ ነው፡፡

## ለ/ <u>የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት የተለያዩ የመሥሪያ ክፍሎች</u>

የአንድ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት ስፋትና ይዘት እንደየት/ቤቱ ተማሪዎች ብዛትና የሚያስተግናደው የክፍል ደረጃ የሚለያይ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት የሚከተሉት የመገልገያ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

- የመጻሕፍትንና የመጽሔቶችን መደርደሪያዎች ጭምር የሚይዝ ስፋቱ 10 ሜ X 20 ሜ = 200 ካሬ ሜትር የሆነ የማንበብያ ክፍል፣
- ለመጽሐፍ መዋሻና መቀበያ ስፍራ 30 ካሬ ሜትር፣
- ስፋቱ 5 ሜ X 8 ሜ. = 40 ካሬ ሜትር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የቤተ መጻሕፍት ሥራ ማከናወኛ ክፍል፣
- አዳዲስ መጻሕፍትና መጽሔቶች ማስታወቂያ ስፍራ 9 ካሬ ሜትር፣
- ለት/ቤቱ ስታፍ (staff) አባላት ማንበቢያ ስፍራ 20 ካሬ ሜትር፡፡

## ሐ/ <u>ቤተ መጻሕፍት መያዝ ያለበት ክምችት</u>

ለሰው ልጅ የመረጃና የዕውቀት ምንጭ ከሆኑት ነገሮች መካከል በዋናነት መጻሕፍት ናቸው፡፡ ሰዎች መፃሕፍትን በማንበብ ስለዓለምና ስለራሳቸው የሚኖራቸው የግንዛቤ አድማስ ያሰፋሉ፡፡

ስለሆነም አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት ለመማር ማስተማሩ ተግባር ድጋፍ የሚሰጡ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተጻፉ መፃሕፍት፣ ሞኖግራፎች (monograph)፣ በተከታታይ የሚታተሙ መጽሔቶች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ የኦዶቪዥዋል ማቴሪያሎች፣ ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ መጻሕፍትና የጥናት ውጤቶች፣ መዝገበ ቃላት፣ መዝገበ ጥበብ አልሚናክ ዓመታዊ ስንክሣር የሕይወት ታሪክ፣ ጋዜጦች፣ በራሪ ጽሑፎችና ካርታዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

## በአንድ ት/ቤት ውስጥ የሚቋቋመው ቤተመጽሐፍት

- ከመማሪያ ክፍሎች የራቀ፣ በማጣቀሻና በክፍል ትምህርት መጻሕፍት የተሟላና የሰለጠነ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡
- የመጻሕፍቱ ብዛትና አይነት ከተማሪ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
- ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በቂ ቅጂ ያላቸውን መጻሕፍት በውሰት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡
- ቤተመጻሕፍቱ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች እንዲገለገሉበት ቀኑን ሙሉ ክፍት መሆን ይኖርበታል፡፡

### 1.13.4. የት/ቤት ማበልጸጊያ ማዕከላት አደረጃጀት

የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ዋና ዋና ዓላማዎች

- የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥናትና በምርምር ለማበልጸግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- ሥርዓተ ትምህርቱን እንደየ አካባቢው ሁኔታ ማዳበር፣
- የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣
- አጫጭር የሙያ ማስተዋወቂያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣
- የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚደግፉ የቤተ መጻሕፍት ዶክሜንቴሽንና የኦዶቪዡዋል አገልግሎቶችን ማሳደግና ማስፋፋት፤

በአጠቃላይ የማዕከላት ዋና ዓላማና ተግባር ከላይ የተገለጹትን በማከናወን ትምህርቱን ተጨባጭ የሚያደርጉ አዳዲስ ዘዴዎችንና ስልቶችን በመቀየስና የፈጠራ ሥራዎችን በማካሄድ ለትምህርቱ ጥራትና ጥልቀት ጠቃሚና ከፍተኛ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

ለዚህም አገልግሎት እንዲያመች በየወረዳው የተጠናከሩና የተደራጁ ማዕከላት እንዲኖሩ የሚደረግ ሲሆን በት/ቤት ደረጃ ደግሞ ከወረዳ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ከላይ የተጠቀሱትን የማዕከላት ዓላማ ተግባራዊ የሚያደርጉ የት/ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ይቋቋማሉ፡፡

ስለዚህ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በሰው ኃይልም ሆነ በማቴሪያል የተደራጀ የማበልፀጊያ ማዕከል ሊኖረው ይገባል፡፡

### 1.13.4.1 በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከማዘጋጀት አኳያ ሊኖር የሚገባው ስታንዳርድ፣

- አንድ ስፋቱ 7 ሜ x 15 ሜ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ ክፍል፣
- አንድ ስፋቱ 7 ሜ x 8 ሜ የሆነ የሥርቶ ማሳያና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማዋሻ ክፍል ሊኖር ይገባል፡፡

### 1.13.4.2. በትምህርት ቤት ማበልጸጊያ ማዕከል ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የእጅ ሥራ መሥሪያ መሣሪያዎች፣

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | ስክሩድራይቨር | 1 |
| 2. | አግድም ቆረጥ መጋዝ | 1 |
| 3. | የብረት መቁረጫ መጋዝ | 1 |
| 4. | መላጊያ ትለቁ | 1 |
| 5. | መላጊያ ትንሹ | 1 |
| 6. | ተጠቅላይ ሜትር /ባለ 3 ማትር/ | 1 |
| 7. | ቲ-ስኳር | 1 |
| 8. | ትራይ ስኳር | 1 |
| 9. | ድሮውንግ ኢንስትሩሜንት | 4 |
| 10. | ፕሮትራክተር | 1 |
| 11. | ትራያንግል ሂሺ ፕላስቲክ 30 60 90 | 2 |
| 12. | ትሪያንግል ሂሺ ፕላስቲክ 45 90 | 2 |
| 13. | የእንጨት መሰርሰሪያ | 1 |
| 14. | የብረት መሰርሰሪያ | 1 |
| 15. | የእንጨት ሞረድ | 2 |
| 16. | የወረቀት መቁረጫ 61 x 61 ሳ.ሜ | 1 |
| 17. | ትልቅ የብረት ማሠሪያ ሞርሣ | 1 |
| 18. | ትንሽ የእንጨት ማሠሪያ ሞርሣ | 1 |
| 19. | የብረት መሞረጃ ሞረድ | 2 |
| 20. | ግራይንደር ቤንች ሃንድ | 1 |
| 21. | የእንጨት መሮ | 1 |
| 22. | ሴክላምፕ | 2 |
| 23. | ፒንሣ | 1 |
| 24. | ማዶሻ | 1 |

### 1.13.4.3 በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ ለየትምህርት ዓይነቱ ሊኖሩ የሚባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

#### 1.13.4.3.1. ለቋንቋ ትምህርት

1. የድምፅ መሣሪያዎች (Audio materials)
2. ቪዡዋል (Visual materials)
3. ቻርቶች (Charts)
4. የቃላት ካርድ (Word Card)
5. ፍላሽ ካርድ (Flash card)
6. ሻሽ ቦርድ (Shash board)
7. ሥዕሎች (Picture cards)
8. ክፍል ሊወሰዱ የሚችሉ ዕቃዎች (Realia)
9. ምልክቶች (Signs)
10. ፊልሞች /የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ

#### 1.13.4.3.2. ለሂሣብ ትምህርት

| No. | Description of Items |
|---|---|
| 1. | Wooden black-board protractor (with handle) |
| 2. | Set square |
| 3. | Chalk compasses |
| 4. | Black-board ruler |
| 5. | Pegboards (for nail boards or geo-board) |
| 6. | Balance (excluded if available in science laboratory) |
| 7. | Plastic graduated beakers and funnels |
| 8. | Geometrical surfaces and solid samples |
| 9. | Graph-board with horizontal and vertical lines at the with-top comer (graph board) |
| 10. | Set of mathematical instruments (students) |
| 11. | Token money (Ethiopia) |
| 12. | Abacus metal or wooden ten parallel wires each line containts too polished wooden heads. |

#### 1.13.4.3.3. ለኅብረተሰብ ትምህርት

1. የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች አትላስ
2. ፖንቶግራፎች
3. ቴርሞሜትሮች
4. የግድግዳ ካርታዎች
   - የዓለም ካርታ
   - የአፍሪካ ካርታ
   - የኢትዮጵያ ካርታ
   - የክልል ካርታ
5. ሌሎች /ግሎቦች/

#### 1.13.4.3.4. ለሥነ ሥዕል ትምህርት

1. ለኮላዥ ሥራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ዕቃዎች
2. ለንድፍ ሥራ " " "

3. ለሕትመት ሥራ " " "
4. ለቅርፃ ቅርጽ ሥራ " " "
5. ለቀለም ቅብ ሥራ " " "

### 1.13.4.3.5. ለሙዚቃ ትምህርት

1. መዝሙሮችና ምቶችን ለማጀብ የሚረዱ የሙዚቃ መሣሪያዎች /ሪትምስቲክ፣ ከበሮ ማራካሻ/ ፀናጽል፣ ትሪያንግል …/
2. የሙዚቃ ኖታዎችን ለማስለየት የሚረዳ የሙዚቃ መሣሪያ

### 1.13.4.3.6. የልዩ ትምህርት ማካሄጃ ተጨማሪ መሣሪያዎች

#### ማየት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- የብሬል ወረቀት
- ስሌትና ስታይለስ
- የብሬል መጻሕፍት
- የብሬል ማስመሪያና ፕሮትራክተር
- አባከስ
- ቴፕሪኮርደርና ካሴት
- የታይፕ መኪናና የቴፕሪኮርደር መለዋወጫ
- ነጭ ባትሪ
- ኣፕታኮን /ዓይነ-ሥውራን ለንባብ የሚረዱበት መሣሪያ/ መጠነኛ የዕይታ ችሎታ ላላቸው
- በቅርበት የሚያሳይ ቴለቪዥን
- ኦቨርሄድ ፕሮጀክተር
- ትልልቅ ስፒል
- ባለትልቅ መስመር ወረቀት
- አጉሊ መነፅር
- ለማንበቢያ የሚረዳ
- የታይፕ መኪናና ቴፕሪከርደር

#### መስማት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሳየት፣
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያለ ነገር እንዲታይ ማድረግ፣
- በከፊል ለሚሰሙት ድምፅ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም፣ ለምሳሌ፡- ረዳት የመስሚያ መሣሪያ፣
- ድምጽ አልባ የታይፕ መኪና መጠቀም፣

<u>ማቴሪያሎች</u>

- የዕይታ መሣሪያዎች፣ ብርሃን አስተላላፊ ወረቀት ፊልምና ካብሸን፣ ስላይድ ፊልምና ቻርት ለማሳያ አስፈላጊ ናቸው፡፡

## 1.13.4.3.7. ለተፈጥሮ ሣይንስ ትምህርት /Science Kit Items For Primary Schools/

| No. | Items | Quantity |
|---|---|---|
| 1. | Peg board stand with base | 1 |
| 2. | Peg boards strip for moments | 1 |
| 3. | Peg board strip | 1 |
| 4. | Pulley-small | 5 |
| 5. | Pulley-combined | 1 |
| 6. | Pulley-combined | 2 |
| 7. | Trolley | - |
| 8. | 10 Grm Mass | 1 |
| 9. | 20 Grm Mass | 2 |
| 10. | 50 grm Mass | 3 |
| 11. | 100 Grm Mass | 2 |
| 12. | Scale Holder | 1 |
| 13. | Block weight | - |
| 14. | Clip-Large | 4 |
| 15. | Clip-small | 6 |
| 16. | Spindle-short 54mm long | 5 |
| 17. | Spindle-long 90 mm long | 2 |
| 18. | Spindle-Conical end 69 mm long | 1 |
| 19. | Bi-convex Lense F 100 mm clear Plastic R 100 mm | 2 |
| 20. | Semi-circular Block R. 30 mm clear plastic | 1 |
| 21. | Bi-concave lense F-clear plastic R 100 mm | 1 |
| 22. | Prism 90 – 45 Clear plastic | 1 |
| 23. | Bi –convex Lense F 50 mm Clear Plastic R, -30mm k2-100mm | 1 |
| 24. | Plane parallel Block-Clear plastic | 1 |
| 25. | Plane Mirror mounted – 60x15 mm | 2 |
| 26. | Curved Mirror | 2 |
| 27. | Angle Bracket | 2 |
| 28. | Iron clip | 1 |
| 29. | Iamination set-30 pieces, mild steel strips 12x65mm | 1 |
| 30. | Battery connector | 6 |
| 31. | Contact Strip-Large | - |
| 32. | Contact Strip-small 90x12mm | 4 |
| 33. | Vibrator-Mild-Steel, 180x12mm | 1 |
| 34. | Strip for magnets mild steel, 50X12m | 1 |
| 35. | Flexible lead 120 mm with wedged ends | 5 |
| 36. | Flexible lead 300 mm “ “ “ | 4 |
| 37. | Flexible lead 500 mm “ “ “ | 2 |
| 38. | Coil 400 turn with square spia forcone | 1 |
| 39. | Bush | 1 |
| 40. | Spring connector | 16 |
| 41. | Plastic sleeve | 1 |
| 42. | Resistance wire-Nichrome 500 mm -100 mm per meter | |
| 43. | Copper wire-Tinned 500 mm | 1 |
| 44. | Copper wire insulated-singlestrand 500 mm | 1 |
| 45. | Moving Iron with pointer | 1 |
| 46. | Riged Plastic -50 mm long 32 mm diameter | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| 47. | “ “ 150 mm “ “ | 1 |
| 48. | Bulb holder – with long leads for optics | 1 |
| 49. | “ “ “ short long for circuit board | 3 |
| 50. | Inclined plane | 1 |
| 51. | Hook for single pully | 1 |
| 52. | “ ‘ double pully | 1 |
| 53. | Coil 30 turns | 1 |
| 54. | String with coxs – 500 mm | 1 |
| 55. | String with Hoozs – 750 mm | 1 |
| 56. | “ “ “ 1000 mm | 1 |
| 57. | “ “ “ 1250 mm | 1 |
| 58. | Joined string with Hooks | 1 |
| 59. | Knurled nut | 25 |
| 60. | Rhehostat | 1 |
| 61. | Plastic Tubing 1/8 100 mm long | 1 |
| 62. | Test tube holder | 1 |
| 63. | Test tube holder base | 1 |
| 64. | Viewer | 1 |
| 65. | Land lens | 1 |
| 66. | Forcens | 1 |
| 67. | Mounted needle | 1 |
| 68. | Universal clip handle | 1 |
| 69. | Plastic Tube -100 mm –Long | 1 |
| 70. | Universal clip | 1 |
| 71. | Plate with slites | 1 |
| 72. | Test tube Brush | 1 |
| 73. | Root marker | 1 |
| 74. | Wooden Block | 1 |
| 75. | Scalpel Handel | 1 |
| 76. | Pointer for expassion experiment | 1 |
| 77. | Current Blance lever | 1 |
| 78. | Asbestos hat 150 mm square | 1 |
| 79. | Copper electrode-cooper tube 80 mm long | 2 |
| 80. | Carbon electrode-carbonrod in copper tube | 2 |
| 81. | Spatila-stair less-140 mm long | 1 |
| 82. | Deflagrating Spoon-stainless 220 mm long | 1 |
| 83. | Beaker – 400 ml | 1 |
| 84. | Dropper | 1 |
| 85. | Themometer | 1 |
| 86. | Set of slides – 13 slides | 1 |
| 87. | Test tube – large | 1 |
| 88. | Test tube disposable | 6 |
| 89. | Filter punnel-plastic | 1 |
| 90. | Petri-Dish | 2 |
| 91. | Syringe 10 ml | 2 |
| 92. | Cork Stopper-large | 4 |
| 93. | Blades for Scalper | 2 |
| 94. | Modeling clay, ½ packet | 1 |
| 95. | Scissors | 1 |
| 96. | Funnel | 1 |
| 97. | Boiling tube | 1 |
| 98. | Screw-long | 2 |
| 99. | Screw-short | 6 |

| | | |
|---|---|---|
| 100. | Plastic cap | 1 |
| 101. | Plastic cap with hole | 1 |
| 102. | Plastic cap with glass tube | 1 |
| 103. | Bulb-round | 3 |
| 104. | Measuing cylinder 50 ml | 1 |
| 105. | Delivery tube glass 245 mm long | 1 |
| 106. | “ “ “ 80 mm long | 2 |
| 107. | Glass rod – 5x140 mm long | 1 |
| 108. | Combustron tube 300 mm long 10-48 dia. | 1 |
| 109. | Measurings silinder 10 ml | 1 |
| 110. | Watch glass -75 mm diameter | 1 |
| 111. | Rubber Bung large with 1 hole | 1 |
| 112. | Rubber Bung large with 1 hole | 1 |
| 113. | “ “ “ “ 2 holes | 1 |
| 114. | “ “ small for 150x16 mm test tube | 1 |
| 115. | “ “ “ with 1 hole | 2 |
| 116. | Cork stopper for 150x16 mm test bue | 6 |
| 117. | Porcalain boat | 1 |
| 118. | Plastic tubing with hole intended dia ¾ for Expansion experiment | 1 |
| 119. | Rubber Bung with glass tube | 1 |
| 120. | Crystalization Dish-plastic bottle 110 mm 2x85 cm Deep | 1 |
| 121. | Boiling flask | 1 |
| 122. | Crocodile clip with 300 mm lead | 2 |
| 123. | Penlight Bulb | 1 |
| 124. | Diode 50 V. lamp | 1 |
| 125. | Dry cell-Di.6V 32mm dia. 55mm long | - |
| 126. | Visking Tubing 15 cm | 2 |
| 127. | Beader – 50ml heat resistant | 2 |
| 128. | magnet – round | 1 |
| 129. | Washer | 6 |
| 130. | Hammer | 1 |
| 131. | Halk saw | 1 |
| 132. | Plier | 1 |
| 133. | Screw driver | 1 |
| 134. | Audus Apparatus | 1 |
| 135. | Kit Box | 1 |

### 1.13.5. የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ክፍል

#### 3.13.5.1. ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ለመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ባለሙያዎች

ተማሪዎች ካላቸው የአካልና የስሜት ዕድገት ባህሪያቸው እና ከትምህርት ቤት ግቢና ከት/ቤት ውጭ በሚፈጠሩ ችግሮች የተነሣ በተለያዩ መንገዶች ለበሽታና ለአደጋ ይጋለጣሉ፡፡ <u>ለምሳሌ</u> ያህል በጨዋታ ሜዳ ላይ እንዲሁም በሥራ ቦታዎች የወለምታ፣ የስብራት፣ የመቁሰልና የመድማት፣ በእባብ የመነደፍና በውሻ የመነከስ፣ በስለት ነገር የመቆረጥና የመወጋት፣ በልዩ ልዩ ሕመሞች ምክንያት

/በስኳር በሽታ በሚጥል በሽታ/ አእምሯቸውን የመሳት፣ በውኃ የመስመጥ፣ የመታፈንና የእሳት አደጋ ሁኔታዎች ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ተማሪ ከፍተኛ የሕመም፣ የጭንቀት፣ የሁከት ሁኔታዎች ይታይበታል፡፡

ይህን በመሳሰሉ ችግሮች ፈጥኖ በመድረስ የሕክምና እርዳታ የሚሰጥ የጤና ባለሙያ በቅርቡ ላይኖር ይችላል፡፡ በአቅራቢያው የጤና አገልግሎት ቢኖርም እንኳን እቦታው እስኪደርስ ድረስ በሽተኛው ሊጐዳ ይችላል፡፡ ሊሞትም ይችላል፡፡

ስለዚህ በት/ቤት ቅጥር ግቢ የሚገኘው የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ ዋና አገልግሎቱ በሽተኛው ሐኪም ቤት ከመድረሱ በፊት ያለውን ችግር ለመቀነስ፣ እንዳይባባስ ለመርዳትና በሕይወት አቆይቶ ለሕክምና ባለሙያ ለማድረስ የሚያግዝ ፈጥኖ ደራሽ የነፍስአድን ሥራ ነው፡፡

በመሆኑም አንድ ት/ቤት ይህን ሥራ ለማከናወን በየት/ቤቱ የሰለጠነ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ሰጪ ባለሙያ፣ የህክምና ዕርዳታ መስጫ መሣሪያዎችና የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል (1st aid post) ሊኖሩት ይገባል፡፡

በአንድ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን (first Aid Kit) ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የሕክምና መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. Adhesive plaster 5 cm x 10 m rolls
2. 12 vow gauze bandage 8 cm x 5 rolls
3. Dissecting foreceps
4. Examination gloves
5. 1 battle dettol 250 ml.
6. Scissers 14 cm Gc.P
7. Elastic bandage 10 cm x 4.5m.
8. 2 elastic woven bandage 8 cm x 5m.
9. 12 vow gauze bandages 7.5 cm x 5m.
10. 4 triangulaire bandages
11. Cotton Wool 400 gm.
12. I pack handy plast ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ቁሳቁሶች ከነሳጥኑ በቀይ መስቀል ማኅበር በኩል ሊገዙ ይቻላል፡፡

ከዚህም በላይ በውስጡ ያሉት ዕቃዎች ሲያልቁ የተወሰነ ገንዘበ ለቀይ መስቀል ማኅበር በመክፈል ማሟላት ይቻላል፡፡ ከ100 በላይ ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶች ሁለት ወይም ሦስት የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ሳጥን ያስፈልጋል፡፡

ሕክምናው ከት/ቤቱ አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ በአቅራቢያ ወደሚገኙ የሕዝብ /ኮሚኒት/ ክሊኒኮች ይላካሉ፡፡

### *1.13.6. ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት መሣሪያዎች*

| ተራ ቁ. | የመሣሪያ ዓይነት | የክፍል ደረጃ | መጠን ክብደት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | <u>ኳሶች</u> | | | | |
| | - የእግር ኳስ | 1-3 | ቀላል የላስቲክ ኳስ | 3 | 1 ለ80 ተማሪዎች |
| | - “ “ | 4-6 | ቁጥር 3 | 3 | 1 ለ80 ተማሪዎች |
| | - “ “ | 7-8 | ቁጥር 4 | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - ቅርጫት ኳስ | 1-4 | ቀላል የሚነጥር ኳስ | 3 | 1 ለ100 “ |
| | - “ “ | 5-8 | ሚኒ ባስኬት ቦል | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - የእጅ ኳስ | 1-4 | ጁኒየር ሳይዝ | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - “ “ | 5-8 | ሲኒየር ሳይዝ | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - መረብ ኳስ | 1-4 | ጁኒየር ሳይዝ | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - “ “ | 5-8 | ሲኒየር ሳይዝ | 3 | 1 ለ80 “ |
| | - ከባድ ኳስ | 1-4 | 2 ኪሎ ግራም | 2 | 2 በአንድ ክፍለ ጊዜ |
| | - “ “ | 5-8 | 3 ኪሎ ግራም | 3 | “ “ “ |
| 2 | <u>የአትሌትክስ መሣሪያዎች</u> | | | | |
| | - ጦር | 4-6 | 500 ግራም | 3 | በአንድ ክፍለ ጊዜ |
| | - “ | 5-8 | 600 ግራም | 2 | “ “ “ |
| | - “ | 5-8 | 700 “ | 3 | “ “ “ |
| | - ደስክስ | 4-6 | 0.75 ኪ.ግ | 3 | “ “ “ |
| | - “ | 7-8 | 1 ኪ.ግ | 2 | “ “ “ |
| | - አለሎ | 4-6 | 3 ኪ.ግ | 3 | “ “ “ |
| | - “ | 7-8 | 4 ኪ.ግ | 3 | “ “ “ |
| | - የከፍታ ዝላይ ቋሚ በጥንድ | 1-8 | ከብረት የተሠራ | 1 | ለት/ቤቱ |
| | - የከፍታ ዝላይ አግዳሚ | 1-8 | | 1 | “ |
| | - የሩጫ ሰዓት | 1-8 | ኤሌክትሮኒክስ | 3 | “ |
| | - የሩጫ ማስነሻ ሽጉጥ | | | | |
| | “ “ ጥይት/በፓኬት/ | 1-8 | | 2 | “ |
| | - ሳንቃ | 1-8 | | 1 | “ |
| | - የሪሌይ ቅብብል ዱላዎች | 1-8 | 28 ሳ.ሜ ርዝመት | 8 | ክብደቱ ከ50 ግራም ካልበለጠ እንጨት ወይም ስስ የብረት ቧንቧ የተሠራ |
| 3 | <u>የጂምናስቲክ መሣሪያዎች</u> | | | | |
| | - ፍራሽ | 1-8 | 12 ሳ.ሜ ውፍረት 1x3 ሜትር | 3 | ለት/ቤቱ |
| | | 1-8 | | 3 | “ |

| ተራ ቁ. | የመሣሪያ ዓይነት | የክፍል ደረጃ | መጠን ክብደት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | - ተደራራቢ ሣጥን<br>- በክ<br>- አግዳሚ ወንበር /ቤንች/<br>- ቀለበቶች | 1-8<br>1-8<br>1-8 | ½ ሜትር ሬዲየስ | 1<br>2<br>20 | “<br>“<br>“ |
| 4 | **ሌሎች**<br>- ለመውጣት ለመውረድ የሚያገለግሉ ገመዶች<br>- የመዝለያ ገመድ<br>- ለኢላማ መምታትና ለልዩ ልዩ ጨዋታዎች ማከናወኛ<br>- ለኢላማ የሚያገለግሉ ሶኬትልስ<br>- የካኪ ጨርቅ ከረጢቶች<br>- የመምህሩ ቱታ<br>- ሽራ ጫማ<br>- ፊሺካ<br>- የኳስ መንፊያ ፓምፕ<br>- የመረብ ኳስ መረብ<br>- የባስኬት ቦል ቋሚ ከነሣንቃ ውና ከነቀለበቱ በጥንድ<br>- መለኪያ ሜትር<br>- የስፖርት ሹራብ /ማሊያ/ ከነቁምጣው | 1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8 | 8 ሜትር ቁመት<br>7 ሣ.ሜ. ውፍረት<br>1.50 ሜ ርዝመት<br>አነስተኛ መጠን ያላቸው ከፕላስቲክ የተሰሩ ኳሶች<br>20 x10 ሚ.ሜ<br>የሀገር ውስጥ<br>“ “<br>የሀገር ውስጥ<br>ባለ 50 ሜትር | 20<br>20<br>10<br>1<br>2ጥንድ<br>2<br>2<br>2<br>1<br>1<br>16 | ለት/ቤቱ<br>ከእንጨት ወይም ከፕላስቲክ የተሠራ ሰአሸዋ የተሞሉ በዓመት<br>ለት/ቤቱ<br>“<br>“<br>“<br>“ |
| 5 | **የስፖርት ሜዳዎች**<br>- የእግር ኳስ ሜዳ<br>- የቅርጫት ኳስ ሜዳ<br>- የእጅ ኳስ ሜዳ<br>- የመረብ ኳስ ሜዳ<br>- የከፍታ ርዝመት መዝለያ | 1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8<br>1-8 | 110x90= 9900 ካ.ሜ<br>20x16 = 448 ካ.ሜ<br>42 x 22 = 924 ካ.ሜ<br>20 x 11 = 220 ካ.ሜ<br>20 x 15 =420 ካ.ሜ | | የሩጫ መስመሮችን ያጠቃልላል |

## 1.14. የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ መለኪያ /ስታንዳርድ/

ተማሪዎች በተዘጋጀላቸው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የደረጃውን ትምህርት ማጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ ት/ቤቶች የሚከተሉትን መንገዶች ይከተላሉ፡፡

- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ትምህርት ቀድሞ በተቀመጠው ክ/ጊዜና የትምህርት ወቅት ተገኝተው መማራቸውን ያረጋግጣሉ፡፡

- ተከታታይ ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና መውሰዳቸውን እና በዝውውር ፖሊሲው መሠረት ወደ ሚቀጥለው ክፍል ለመግባት የሚያስችልና "የነበሩበትን ክፍል አጠናቋል" የሚል አጥጋቢ ውጤት ማምጣታቸውን ይረጋገጣል፡፡
- ለክፍል ደረጃውና ለእርከኑ የተመደበውን ትምህርት ተማሪዎች በትክክል ማጠናቀቃቸውን በት/ቤቱ ወይም በብሔራዊ ፈተና ውጤት ይረጋገጣል፡፡

### *1.14.1. በየክፍል ደረጃውና በየእርከኑ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች*

- በየዓመቱ የክፍል ትምህርት ማጠናቀቂያ ወይም የሴሚስቴር ፈተና ውጤት መግለጫ ወይም የተጣራ ሪፖርት ካርድ ለተማሪ ይሰጣል፡፡
- የአንድን እርከን ትምህርት ሳያጠናቅቅ በየእርከኑ መካከል ተማሪው ት/ቤት ቢቀይር ከሚለቅበት ት/ቤት የሚሰጠው ዝርዝር ውጤት የየክፍሉ የተጠናቀረ እና የመልቀቂያ /ትራንስክሪብት/ ህጋዊ ሠርቲፊኬት የተወሰነ የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡
- በየእርከኑ መጨረሻ ክፍል የሚሰጥ የትምህርት ውጤት ህጋዊ መግለጫ /ትራንስክሪብት/ እና የብሔሪዊ ወይም ክልላዊ ፈተና የሚሰጥበት ደረጃም ከሆነ የብሐራዊ ወይም የክልላዊ ፈተና ውጤት ህጋዊ መግለጫ ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መብቃታቸውን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡
- በየአርከኑ መጨረሻ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ወይም ሰርቲፊኬቶች በማስተማሪያ ቋንቋ በአገር አቀፋዊ የሥራ ቋንቋ ወይም በክልላዊ የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው ይሰጣሉ፡፡

## 1.15. በየእርከኑ መጨረሻ የሚጠበቁ የተማሪዎች ፕሮፋይል /ባህሪያት/

### *1.15.1 የመጀመሪያ ደረጃ የአራት አመት ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ባህሪያት /1-4/*

- ደረጃውን የጠበቀ የእጅ ጽሑፍ የማንበብና መሠረታዊ ስሌት ችሎታዎች ይኖራቸዋል፡፡
- ስለራሳቸው ማንነትና ምንነት፣ ስለቤተሰባቸውና ህብረተሰቡ ኃላፊነቶችና ችግሮች መጠነኛ ግንዛቤ አላቸው፡፡ የአቅማቸውን ያህል ኃላፊነት ይሰማቸዋል፣ ችግሮችንም ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
- ስለ ተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች ምንነት ጠቃሚነትና እንክብካቤ ያውቃሉ፣ በተግባር ይገልፃሉ፣ ያሳያሉ፡፡

- በአካባቢው ያሉትን የሥራና የምርት እንቅስቃሴዎችን ያስተውላሉ፣ ይገነዘባሉ፣ በሚፈልጓቸው የሥራ ዘርፎች ይሳተፋሉ፡፡
- በግለሰብ፣ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ጐጂና ጠቃሚ የሆኑትን አመለካከቶች፣ እምነቶች አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ይመረምራሉ፣ ያነፃፅራሉ፣ ይመርጣሉ፡፡
- አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሟአቸው ለመጠየቅና ለመረዳት ይፈልጋሉ፣ ባገኙት ምክርም ለመጠቀም ይጣጣራሉ፡፡
- ከችሎታውና ከአቅማቸው ጋር የሚጣጣሙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን የመሞከርና የመለመማድ ከፍተኛ ፍላጐት ያሳያሉ፡፡
- የግልና የአካባቢ ንጽህና ይጠብቃሉ፡፡
- ተግባርን በተናጠል ከመፈፀም ፋንታ እንዲተገቢነቱ በመስተጋብሮታዊ ተሳትፎ በጋራ ክንዋኔ ለጋራ ውጤት የመሰለፍ ስልትን ይለማመዳሉ፡፡

## *1.15.2. የመጀመሪያ ደረጃ የስምንት ዓመት ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች /ባህሪያት/ /1-8/*

- ለቀላል ሥራ ዝግጁ ናቸው፡፡
- በእውቀትና በሙያ ዘርፎች መጠነኛ አጠቃላይ ግንዛቤንና ክሂሎትን የጨበጡ በመሆናቸው ለብዙ አይነት ስልጠናዎች የተዘጋጁ ይሆናሉ፡፡
- የእደጥበብ ችሎታዎች፣ የእጅ መሣሪያዎችና የቀላል መኪኖች አጠቃቀም ክሂሎት፣ የሥራ ሂደት እውቀት ስላላቸው በሥራ ላይ መመሪያ፣ ሥልጠናና ተከታታይ ድጋፍ እየተሰጣቸው ቁጥጥር እየተደረገ አምራች ሠራተኞች ይሆናሉ፡፡
- በየደረጃው ኃላፊነት የሚሰማቸው ስለሆኑ ንቁ ባህላዊ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡
- በተከታታይ ትምህርት አማካኝነት የአውቀት አድማሳቸውን ለማስፋት ክሂሎትን ለማዳበር፣ አስተሳሰብን ለማጐልበት የእደ ጥበብ ችሎታን ለማሻሻል ይችላሉ፡፡
- በጋራ ክንዋኔ ለጋራ ውጤት በመስተጋብሮታዊ ተሳትፎ የመሰለፍ ልምድን ያዳብራሉ፡፡